ወርኃዊ ጥንቅር፣ ቁ.006
ነሐሴ 2017 ዓ.ም.



# የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ክራሞት

## እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

research@bridge-et.org

BRIDGE Research & Innovation- Parliaments. Peace. Policy

## መልክዓ-ብሪጅ

መቀመጫውን አዲስ አበባ ያደረገ፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዐዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሰረት አገር በቀል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ሆኖ የተመዘገበ የጥናትና ምርምር ተቋም ነው። ብሪጅ፣ በዋናነት በኢትዮጵያ እና በምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) አባል አገራት ውስጥ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እንዲጎለብት እና ሰላም እንዲበለጽግ የሚሠራ ገለልተኛ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ ፖሊሲ ተኮር የጥናት እና ምርምር ተቋም ነው።

## ተልዕኮ

ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ይጎለብት ዘንድ፣ ለፖሊሲ አወጣጥ ግብዓት የሚሆኑ፣ ተጨባጭነት ያላቸው ምርምሮችን ማድረግ እና የፖሊሲ ምክረ ሐሳቦችን ማቅረብ፤

## ርዕይ

በሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች እና በቀጠናዊ የሰላም፣ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰዋዊ እና ቁሳዊ ልማት ላይ፣ በኢጋድ ቀጠና ተቀዳሚ የምርምር እና ፖሊሲ አመንጪ ማዕከል መሆን፤

## መሠረታዊ ዕሴቶች

- አጽንዖተ ትኩረት፦ ከፍተኛ ትኩረት የተሰሩ እና ተጨባጭነት ያላቸው ጥናት ምርምሮችን ማቅረብ።
- አዲስነት፦ ለዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ተግዳሮቶች ፈጠራዊ እና ተለዋዋጭ መፍትሔዎች የታከለባቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች ማዋጣት
- ታማኝነት፦ ተዓማኒነት ያላቸውን የምርምር ውጤቶችን በማቅረብ ተዓማኒነትን መጠበቅ

## ግቦች

ኢትዮጵያ እና በኢጋድ ቀጠና የሚገኙ የፌዴራል እና የክልል ፓርላማዎች በሚከተሉት መንገዶች ማጠናከር

- ተጨባጭ ምርምሮችን መከወን
- የእንደራሴዎችን ብቃት ለማሳደግ የዐቅም ግንባታ ድጋፎችን ማድረግ
- ተጠያቂነትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች ክንውኖችን መከታተል


+251 911 86 12 34

+251 115 57 74 96


research@bridge-et.org

https://bridge-et.org/

150096, Addis Ababa, Ethiopia.

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.









# ማውጫ


የኢትዮጵያ እንደራሴዎች የወርኃ ነሐሴ ክራሞት ........ 1

የእንደራሴዎቹ የውክልና ሥራ ........ 2

የፓርላማ ዲፕሎማሲ ........ 12

የብሪጅ አጭር ዳሰሳዊ ምልከታ በእንደራሴዎቹ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ዙሪያ ........ 15

# የኢትዮጵያ እንደራሴዎች የወርኀ ነሐሴ ክራሞት

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ ወርኀ ነሐሴን ያሳለፉት በዋናነት የሕዝብ ውክልና ሥራቸውን በመተግበር ነበር። ያም ሆኖ፣ በዚኹ ወር ሣሥት ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ሥራዎችን አከናውነዋል። ይኽች የእንደራሴ ሥድስተኛ ዕትምም፣ እነዚያን ብዙዎቹን ክልሎቹ የሸፈኑትን የውክልና ሥራዎች በ'የክልሎቹ እንደሚከተለው ከማወቀሯ ባሻገር፣ ወሩ የዓመቱ መጠናቀቂያ ለመሆን የተቃረበ ነውና፣ በእንደራሴዎቹ የፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ዙሪያ አጠር ያለ ወርኃዊ ዳሰሳዋን እነሆ ብላለች።

# የእንደራሴዎቹ የውክልና ሥራ

የኢፌዲሪ እንደራሴዎች፣ ከሐምሌ እስከ መስከረም መጨረሻ ሳምንት ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ዋናው የውክልና ሥራ እንደመሆኑ፣ እንደራሴዎቹ ወደ ‘ምርጫ ወረዳዎቻቸው በመሄድ የወከሏቸውን የማወያየት እና ጥያቄዎቻቸውን የመስማት ተግባራቸውን፣ በወርኃ ነሐሴ በስፋት ከውነዋል።



የተከበሩ ዶ.ር. መለስ ጡሚሶ በውክልና ሥራቸው ላይ፤

## የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መራጮች ምን አሉ?

በወርኃ ነሐሴ መጀመሪያ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በወልቂጤ ከተማ የተገኙት ኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደራሴዎቹ የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም አለማየሁ እና የተከበሩ ዶ.ር. ታደለ ቡራቃ፣ አንድ ሰፋ ያለ የውይይት መድረክ አዘጋጅተው እንደነበር የምክር ቤቱ መረጃ ያሳያል። በውይይት መድረኩም፣ ለፌዴራል አሥፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች በቀረቡ ጥያቄዎች እና በተመለሱ ምላሾች እንዲሁም በበጀት ዓመቱ ምክር ቤት ያከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራት ቀርበው ዉይይት ተደርጎባቸዋል ተብሏል። ወደ ጠምበሮ ምርጫ ክልልም ብቅ ያሉት እንደራሴው፣ ማንኛውንም ጥያቄ በሰላማዊ መንገድ የመጠየቅ ሕገ-መንግሥታዊ መብት እያለ ሕገ-ወጥ መንገድን ምርጫቸው የሚያደርጉ አካላት መንገዳቸውን በማስተካከል ለሕዝብ ሰላም ቅድሚያ መስጠት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል ተብሏል፡፡ በማረቆ ልዩ ወረዳ በቆሼ ከተማ ውስጥ በሚገኙት ስድስቱም ቀበሌዎች ከተወጣጡ ነዋሪዎች ጋር ውይይት መካሄዱን መናገራቸውን የጠቀሱት ደግሞ የተከበሩ ዶ.ር. መለሰ ጡሚሶ ናቸው። እንደራሴው፣ የተፈጠረው አንፃራዊ ሠላም በፀረ ሰላም ኃይሎች እንዳይደፈርስ ሠላሙን የበለጠ ለማፅናት ሕዝቡ ከመንግስት ጎን ሆኖ ማገዝ እና መደገፍ ይገባል ብለዋልም ተብሏል። ከዚኽ ባለፈ፣ በመስቃን እና ማረቆ ቁጥር 2 ምርጫ ክልል መራጮቻቸውን ያወያዩት እንደራሴው፣ በየደረጃው ያሉ የምክር ቤት አባላት የሕዝብ ተወካዮች እንደመሆናቸው ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር በቅርበት በመገናኘት ለልማት እና የመልካም አሥተዳደር ችግሮቻቸው መፈታት የበኩላቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል ማለታቸውም ተዘግቧል።

በዚያው ወረዳ ከእርሳቸው ጋር የተገኙት ሌላይኛው እንደራሴ የተከበሩ ወ/ሮ ወሰኔለሽ ሆሪያ፣ ከልዩ ወረዳው ባላድርሻ አካላት ጋር በመሆን በኅብረተሰቡ ተሳትፎ እየተገነባ ያለውን የገራድ ቢመዶ አጠቃላይ ሆስፒታል፣ የሰሜን ቆሼ የውኃ ፕሮጀክት እና የቆሼ ጤና ጣቢያ አገልግሎት አሰጣጥን ተዘዋውረው ተመልክተዋል። ነሐሴ 9 2017 ዓ.ም. በክልሉ ሀዲያ ዞን ኮንተብ 02 ምርጫ ክልል በምሻ ወረዳ በሞርሲጦ ከተማ የደረሱት እንደራሴው የተከበሩ ደሳልኝ ኤርሶ፣ ከተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ከተወጣጡ ተሳታፊዎች ጋር መወያየታቸው ሲዘገብ፤ የመወያያ ርዕሰ-ጉዳዮቹም ሠላም፣ የመሠረተ-ልማት አለማሟላት እንዲሁም የማኅበራዊ እና መልካም አሥተዳደር ጉዳዮች ነበሩ ተብሏል። ባለፉት ወራት ከትምህርት፣ ጤና፣ ከንጹሕ መጠጥ ውኃ እንዲሁም ከመንገድ ተደራሽነት አኳያ ሰፋፊ ስራዎች መሰራታቸው የተጠቀሰበት የመራጭ-ተመራጭ የውይይት መድረክ የተካሄደው ደግሞ፣ እንደራሴው ዶ.ር. መሀመድ ሽኩር በመሩት በአልቾ ውሪሮ ወረዳ የተከናወነው ውይይት መሆኑን የምክር ቤቱ ዘገባ ያመለክታል።

በጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ አነሳሽነት በሌሞ ወረዳ ዱባንቾ ቀበሌ የተጀመረው የገጠር ኮሪደር ልማት፣ አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ያደረገ እና የአካባቢውን ገጽታ ከመቀየር ባለፈ ለበርካታ የገጠር ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠር እንደቻለ ማረጋገጣቸውን መናገራቸው የተጠቀሰው የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም አለማየሁ መሆናቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ሲጠቅሳቸው፤ በዚያው ዞን ጊቤ ወረዳ ከእናቶች ጋር ውይይት አድርገዋል የተባሉት የተከበሩ ሙሉነሽ ላሞሬ በበኩላቸው፣ የእናቶች እና ሕፃናትን ጤና ማስጠበቅ ለአገር ኢኮኖሚ ከፍተኛ ሚና አለው ብለዋል ተብሏል። ለዚኹ ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነታቸው ወደ ሙዱላ ከተማ ብቅ ያሉት፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ የማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው ዶ.ር. ታደለ፣ የጠምባሮ-ሙዱላ ሆስፒታል በየካቲት ወር ከነበረበት ለሥራ ያልተመቸ ሁኔታ ተላቆ የሕክምና ባለሙያዎች የሚሰሩበት ጽዱ አካባቢ እና ለታካሚዎች ምቹ ማረፊያ የፈጠረ ማሻሻያ መከናወኑንም አንስተዋል ተብሏል። ወደ ጠምባሮ ልዩ ወረዳም የተሻገሩት እንደራሴው ዶ.ር. ታደለ፣ በሕዝብ የተነሱ በርካታ ጥያቄዎችን መንግሥት ምላሽ እንዲሰጥበት በየደረጃ ላለው የመንግሥት አሥፈጻሚ እንደሚያቀርቡ ለሕዝቡ አብራርተዋል፡፡

በዚኹ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሀዲያ ዞን ሾኔ ከተማ፣ ለውክልና ሥራ ክንውን የሄዱት የተከበሩ ወ/ሮ ነቢያት ጥላሁን፣ ከወከላቸው ኅብረተሰቡ ከተወጣጡ አካላት ጋር በሰላም፣ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ፣ በመሠረተ ልማት፣ በሥራ ዕድል እና በመልካም አሥተዳዳር ጉዳዮች ዙሪያ ሰፋ ያለ ውይይት ማድረጋቸውን ገልጸዋል ተብሏል። በዚኹ ዞን ምዕራብ ባዳዋቾ ወረዳ የደረሱት የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም አለማየሁ በበኩላቸው፣ በወረዳው የሚገኙትን የተለያዩ የመንገድ ፕሮጀክቶችን የግንባታ አፈጻጸም እና የጤና ተቋማትን አገልግሎት አሰጣጥ ተዘዋውረው ሲጎበኙ፤ በወረዳው እየተገነቡ ያሉ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ተጠናቀው አገልግሎት እንዲሰጡ ከፍተኛ ጥረት መደረግ እንዳለበት ማሳሰባቸው ተጠቅሷል። እንደራሴው ዶ.ር. አብርሃም፣ በሆሳዕና ከተማም ተገኝተው፣ የሕዝቡን የልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎችን ለመፍታት በዞኑ የተሰሩ ሥራዎች ተስፋ ሰጪ በመሆናቸው ተጠናክረው መቀጠል እንደሚገባቸውም አክለው አሳስበዋል። ሻሾጎ ወረዳ የሄዱት የተከበሩ ወ/ሮ ወርቅነሽ መሐመድ ደግሞ፣ ከወረዳ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በጠቅላይ ሚንስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ አነሳሽነት፣ ‘አንድ ፕሮጀክት ለአንድ መዋቅር’ ዕቅድ መሠረት በፌዴራል መንግሥት በጀት እየተሰራ ያለውን የቦዮ ተፋሰስ ልማት ፕሮጀክት ጎብኝተዋል።

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ከሚገኙት ዞኖች መካከል አንዱ ወደሆነው ጉራጌ ዞን የደረሱት የተከበሩ አቶ ሺሰማ ገብረ ሥላሴ፣ የሕዝቦች ኅብረ-ብሔራዊ አንድነትን የሚያጠናክሩ፣ አገራዊ ልማቱን የሚያፋጥኑ እና የማሻሻያ አጀንዳዎችን የሚያሣልጡ ሕጎች በማውጣት ረገድ እያደረጓቸው ያሉ ጥረቶችን በተመለከተ መረጃዎችን ለተወያዮቻቸው አስገንዝበዋል ተብሏል። ወደዚያው ዞን ምሥራቃዊ ክፍል የሄዱት የተከበሩ ወ/ሮ እፀገነት መንግስቱ፣ ፕሮጀክቶችን ጀምሮ በአጭር ጊዜ ውስጥ የመጨረስ ልማድ የብልጽግና ፓርቲ መለያ ባህሪ እንደሆነ ሲናገሩ ተደምጠዋል፤ ቡኢ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታልንም ጨምረው የጎበኙት እንደራሴዋ፣ ሆስፒታሉ የተሻለ አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝ ገልጸዋል ተብሏል። በምስራቅ ጉራጌ ዞን በምስራቅ መስቃን ወረዳ የተሠሩ ፕሮጀክቶች እጅግ አበረታች ውጤት እያመጡ መሆኑን ገልጸዋል። በቡታጅራ ከተማ ተገኝተው ነዋሪውን ያወያዩት የተከበሩ ወ/ሮ ወርቅነሽ ጀማል በበኩላቸው፣ በውይይቱ ወቅት የተነሱት ጥያቄዎች ለሚመለከተው አካል እንደሚቀርቡ እና ለተፈጻሚነቱም በትኩረት እንደሚሰራ ተናግረዋል ተብሏል። ወደ መስቃን ማረቆም ሻገሩ ያሉት እንደራሴዋ፣ ከተማዋ ለነዋሪዎች ምቹ እና ተስማሚ እንዲሁም ለቱሪዝም መዳረሻ እንድትሆን በተሰራው ሥራ የአመራሩ ትጋት እና የሕዝቡ ቁርጠኝነት የታየበት ነው ማለታቸውም ተዘግቧል። በዚኹ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የሚገኘውን የአንጋጫ ኮንስትራክሽን እና ኢንዱስትሪያል ኮሌጅን የጎበኙት የተከበሩ ዶ.ር. ቤዛ ተሾመ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማረጋገጥ የቴክኒክ እና ሙያ ኮሌጆች የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ የላቀ መሆኑን በማንሳት፣ ኮሌጁ የተቋቋመለትን ዓላማ እንዲያሳካ የባለድርሻ አካላት ድጋፍ እና ክትትል ወሳኝ መሆኑን ሲጠቅሱ፤ እዚያው የሚገኘውን የአንጋጫ መጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታልንም በጎበኙበት ወቅት፣ አልትራሳውንድ እና ሌሎች የህክምና ማሽኖችን ከጤና ሚኒስቴር እና ከጴጥሮስ ሆስፒታል በተገኘ ድጋፍ መበርከቱን ተናግረዋል ተብሏል።

በማዕከላዊው ክልል ከሚገኙት ዞኖች ሌላይኛውን ከምባታ ዞንን የጎበኙት የተከበሩ አቶ ተሾመ ሄራሞ፣ በሁሉም ሴክተር መሥሪያ ቤት ምላሽ ማግኘት ያለባቸውን ጥያቄዎች እያንዳንዱ ሴክተር አቅዶ መስራት እንዳለበት እና በወረዳ፣ በዞን፣ በክልል እና በፌዴራል ደረጃ መመለስ ያለባቸውን ጉዳዮች በተወካዮች በኩል ምላሽ እንዲያገኙ ክትትል እንደሚደረግ መግለፃቸውን ከምክር ቤቱ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል። ወደ ስልጤ ዞን የተሻገሩት የተከበሩ ወ/ሮ ነጃት ሀንዳርሶ በተራቸው፣ በሳንኩራ ወረዳ ደረጃ እየተሰሩ ያሉ የተለያዩ የልማት ስራዎችን እና የድጆ ድልድይን ከዋናው አስፋልት የሚያገናኘውን የዩራፕ የመንገድ ግንባታ የሚገኝበትን ደረጃ ተዘዋውረው መጎብኘታቸው ሲዘገብ፤ በወረዳው ባለፉት ዓመታት ከትምህርት፣ ከጤና፣ ከንጹሕ መጠጥ ውኃ እንዲሁም ከከተማ መሠረተ-ልማት ተደራሽነት አንጻር ሰፋፊ ስራዎች መሰራታቸውን ገልጸዋል።

በጉራጌ ዞን በምሁር አክሊል ወረዳ ለውክልን ግብራቸው ለሄዱት የተከበሩ፣ አቶ ባርጠማ ፍቃዱ፣ በወረዳው በመንገድ፣ በትምህርት፣ በውኃ፣ በጤና እና በግብርና ዘርፎች መሻሻል በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ የሚመለከታቸው አካላት በትኩረት ሊሰሩ ይገባል ሲሉ የውይይቱ ተሳታፊዎች አንስተውላቸዋል ተብሏል። በአካባቢው የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት፣ ተደራሽነት እና የአገልገሎት አሰጣጥ የከፋ ችግር ሆኖ መቆየቱ የተነሳበትን የመራጭ-ተመራጭ የውይይት መድረክ የመሩት ደግሞ፣ በጉራጌ ዞን እዣ ወረዳ ለውክልና ሥራ ብቅ ያሉት የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም በርታ ሲሆኑ፤ ሀባ ቁሊቶ ከተማ የሄዱት ሌላይኛዋ እንደራሴ ዶ.ር. ነጃት ግርማም፣ ከዓመት በፊት ያስጀመሩትን የሕጻናት ማቆያ እና ከሱስ ማገገሚያ ማዕከል የደረሰበትን ደረጃ መጎብኘታቸው ተጠቅሷል፤ በሕዝብ ተሳትፎ የሚሰራውን ኢንተርናሽናል ስቴድየሙንም የጎበኙት እና ወደ አቶቲ ኡሎ ወረዳም ብቅ ያሉት እንደራሴዋ ነጃት ግርማ፣ የለውጡ መንግስት ለሕዝቡ የገባውን ቃል እየፈጸመ፣ ከሕዝብ የሚነሱ የመሠረተ-ልማት እና መልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች እልባት እንዲያገኙ በትኩረት እየሰራ መሆኑን ከማስገነዘባቸው ባለፈ፣ አገር ከውጭ ነባራዊ ኹኔታ ጫና እንዲሁም ከውስጥ ባሉ ጫናዎች ተወጥራ እና የውጭ የእርዳታ መስመሮችም እየተቋረጡ ባለበት ያሉ ችግሮን ለመፍታት እና ለቀጣይም ለመዘጋጀት አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ላይ በትኩረት እየተሰራ ይገኛል ብለዋል ተብሏል።

ከሻሸጎ ወረዳ መለስ ብለው ወደ ሀዲያ ዞን አንሌሞ ወረዳ የወረዱት የተከበሩ የተከበሩ ወ/ሮ ወርቅነሽ መሐመድ፣ በተደጋጋሚ በሚነሱ በሰላም እና ፀጥታ፣ በመልካም አሥተዳደር፣ በመሠረተ-ልማት እና በፕሮጀክቶች አፈፃፀም ዙሪያ ከመራጮቻቸው ጋር ሲወያዩ፤ በሀዲያ ዞን በምሥራቅ ባደዋቾ ወረዳም፣ በኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ስብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም አለማየሁ እና የተከበሩ ወ/ሮ ነቢያት ጥላሁን፣ ከወከላቸው ኅብረተሰብ ከተወጣጡ አካላት ጋር በሰላም፣ በኢኮኖሚያዊ፣ በማኅበራዊ፣ መሠረተ-ልማት፣ በሥራ ዕድል ፈጠራ እና በመልካም አሥተዳደር ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት ማድረጋቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ያሳያል። ወደ ሲራሮ ባደዋቾ ወረዳም ደረስ ያሉት እንደራሴዋ ነቢያት ጥላሁን፣ በወረዳው ያለውን የንጹሕ መጠጥ ውኃ ችግር ለመቅረፍ እየተሰሩ ያሉ የልማት ሥራዎች አበረታች መሆናቸውን ገልጠዋል ተብሏል። ባለፉት የለውጥ ዓመታት በምርጫ ክልሉ በሁሉም መስኮች የተመዘገቡ ውጤቶች አበረታች ቢሆኑም፣ ለዘመናት ጥያቄ ይነሳባቸው የነበሩ የመሠረተ-ልማት ጉዳዮች ዛሬም መፍትሔ እንዳልተሰጣቸው የተነገረበትን የጊሚቢቹ ከተማን የመራጭ-ተመራጭ የውይይት መድረክ የመሩት ደግሞ የተከበሩ አቶ አቤንዔዘር በቀለ ናቸው ተብሏል። በክልሉ ሀዲያ ዞን ኮንትብ 03 ምርጫ ክልል ለሄዱት የተከበሩ ወ/ሮ ሙሉነሽ ላሞሬ፣  ከማዕድን ልማት እንዲሁም ከሠራተኛ ደመወዝ እና የዕዳ ሽግሽግ ጥያቄ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች እርሳቸው በመሩት የውይይት መድረክ ላይ መነሳቱ ተጠቅሷል።

## ከአማራ ክልል ምን ጉዳይ ተነሳ?



በኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህልና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባል የተከበሩ ወ/ሮ ገነት ቤተ በአማራ ክልል የደብረብርሃን ምርጫ ክልል በደብረብርሃን ጤና ጣቢያ እና ጤና መምሪያ የተሰሩ ሥራዎችን እና አገልግሎት አሰጣጣቸውን ሲመለከቱ

በወርኃ ነሐሴ፣ ወደ በአማራ ክልል በመጓዝ ቀዳሚውን የውክልን ሥራቸውን የከወኑት የተከበሩ ዶ.ር. ማኅተመ ኃይሌ ሲሆኑ፣ በደሴ ከተማ ፆታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች የማገገሚያ ማዕከል ለመገንባት በሴቶች እና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ከኹለት ዓመታት በፊት የመሰረት ድንጋይ የተቀመጠ ቢሆንም፣ እስከ አሁን ድረስ ግንባታው ያልተጀመረ በመሆኑ ግንባታውን ለመገንባት ኃላፊነት የወሰደው አሥፈጻሚ አካል በአፋጣኝ ወደ ግንባታ ሊገባ እንደሚገባ አመልክተዋል ተብሏል። ከዚኽ ባለፈም፣ በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም እንዲመጣ በአገራዊ ምክክር ኮሚሽን በኩል እየተፈፀመ ያለው ተግባር የደረሰበትን ደረጃ እና በቀጣይ በአገር አቀፍ ደረጃ በሚደረገው ውይይት የከተማው ነዋሪዎች ማድረግ ስለሚጠበቅባቸው ድጋፍ ለተስብሳቢዎቹ አስገንዝበዋል። ወደ ደብረ ብርሃን ክልል የተጓዙት የተከበሩ ወ/ሮ ገነት ቤተ በበኩላቸው፣ የደብረ ብርሃን ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሪፈራል ሆስፒታል ቀደም ሲል ቅሬታ ይነሳበት የነበረውን የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር በቴክኖሎጂ ታግዞ አሰራሩን በማዘመን ቅሬታውን ደረጃ በደረጃ መፍታት መጀመሩን ተመልክተዋል ተብሏል። እንደራሴዎ፣ በዚያው ከተማ ከሚገኘው ጫጫ ክፍለ-ከተማ ነዋሪ ጋር ከመያያታቸው ባለፈ፣ በማኅበረሰቡ የተጠየቁ የልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች በየደረጃው ላሉ አሥፈፃሚ አካላት በማቅረብ እና በመከታተል ምላሽ እንዲያገኙ በቀጣይም እንደሚሰሩ መናገራቸውን የምክር ቤቱ የዜና ምንጭ ዘግቧል። በዓመት ኹለት ጊዜ ወደ ተመረጡበት አካባቢ በመሄድ የሚያከናውኑት የሕዝብ ውክልና ሥራ፣ በምክር ቤቱ የወጡ ሕጎች የሕዝቡን ተጠቃሚነት ስለማረጋገጣቸው ለመፈተሽ እና መሻሻል የሚገባቸውን ሕጎችም ለመለየት እንደሚረዳ መናገራቸው የተዘገበው ደግሞ፣ የተከበሩ አቶ የሱወርቅ ታፈስ በሾላ ገበያ በመሩት የውይይት መድረክ ሲሆን፤ ሰሜን ወሎ የተገኙት የተከበሩ ወ/ሮ ቅድስት አርአያ በበኩላቸው፣ ላሊበላ ከተማ የሚገኘው የማር ሙዚየም ከተቋቋመበት አላማ አንጻር የጊዜ ቆይታው ሰፊ ክፍተት ያለበት በመሆኑ የተሟላ ሥራ እንዲሰራ የሚመለከተው አካል የበኩሉን ሚና እንዲወጣ አሳስበዋል ተብሏል፤ ከዚኽ ባለፈም፣ ላስታ፣ ቡግና እና ላሊበላ ከተማ ከተውጣጡ የማኅበረሰብ ክፍሎች የመራጭ ተመራጭ መድረክ ያካሄዱት እንደራሴዎ፣ ለሰላም መረጋጋት ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ ማሳሰባቸውን ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ይጠቁማል።

## ከኦሮሚያ የተሰሙት. . .




የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የተከበሩ ወ/ሮ ሳዲያ አማን በተወከሉበት ምርጫ ክልል፣ በምስራቅ ባሌ ዞን ለገሂዳ ወረዳ በቤልቱ ከተማ በተካሄደው የመራጭ ተመራጭ መድረክ ላይ

በዓመቱ ዐሥራ ኹለተኛው ወር፣ ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነታቸውን ይወጡ ዘንድ ምስራቅ ጉጂ ዞን የተጓዙት የተከበሩ አቶ ዱቤ ጂሎ፣ ከሕዝብ ለተነሱት በርካታ ጥያቄዎች መንግስት ምላሽ እንዲሰጥ በየደረጃ ላሉት የመንግስት አሥፈፃሚ አካላት እንደሚያቀርቡ ለውይይቱ ተሳታፊዎች መግለፃቸው ተዘግቧል። ለዚኹ የውክልና ሥራ ወደ ምስራቅ ሸዋ ዞን የሄዱት፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባኤዋ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶ፣ በዓመት ኹለት ጊዜ የሚከናወነው የሕዝብ ውክልና ሥራ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚወጡ ሕግጋትን አፈፃፀም ለመፈተሽ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንዳለው የጠቀሱት አፈ-ጉባኤዋ፣ በአፈፃፀም ሂደት አላሰራ ያሉ ሕጎች ካሉም ምክር ቤቱ ለመፈተሽ እና ለማሻሻል ዝግጁ እንደሆነ ተናግረዋል ተብሏል። የተከበሩ አቶ ስንታየሁ ጥላሁንም፣ በመልካም አሥተዳደር ፣ በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና በሰላም ጉዳዮች ከሕዝቡ ለሚነሱ ጥያቄዎች ትኩረት በመስጠት በወቅቱ ምላሽ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ማስገንዘባቸው ሲዘገብ፤ መታሐራን የጎበኙት የተከበሩ አቶ ሹሚ አያኖ በበኩላቸው፣ ከአካባቢው ሕዝብ ጋር በሠላም እና ጸጥታ፣ በልማት፣ በመልካም አሥተዳደር እና አገልግሎት አሰጣጥ እንዲሁም የፕሮጀክቶች አፈፃፀም ጉዳዮች ላይ መክረዋል ተብሏል።

በዚያ ዝናባማ ወርኃ ነሐሴ ወደ ምዕራብ ሸዋ ደንዲ የተሻገሩት የተከበሩ ወ/ሮ አራሬ ሞሲሳ ፣ በወረዳው አሁን የተገኘው ሰላም ቀጣይነት እንዲኖረው ወጣቶች ሚናቸውን በሚገባ እንዲወጡ ከማስገንዘባቸው ባሻገር፣ ከአኒቻ ከተማ ወጣቶች ጋርም በሰላም እና ልማት ላይ ያተኮረ መድረክ አካሂደዋል ተብሏል። በዚያው ኦሮምያ ክልል አርሲ ዞን ለውክልና ሥራቸው ለተገኙት የተከበሩ ዶ.ር. ሐጂ ከዲር፣ ምላሽ ያላገኙ የሕዝብ ጥያቄዎች ዘላቂ መፍትሔ እንዲሰጣቸው ከተወያዮቹ በኩል ተጠይቀዋል ተብሏል። በዚያ የውክልና ሥራቸው የጢቾ ወረዳ ነዋሪዎችንም ያወያዩት እንደራሴው ዶ.ር. ሐጂ፣ የወረዳው የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰት አበረታች ደረጃ ላይ መሆኑን ገልጸው፣ የወረዳው ከተማ አገልግሎትን ለማሳለጥ እና የሥራ ዕድል በበለጠ ለመፍጠር የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰት አቅሞችን ማሳደግ እንደሚገባ መናገራቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ አክሎ ጠቅሷቸዋል። ወደዚያው ዞን የምዕራቡ ክፍል ብቅ ያሉት እንደራሴዋ ወ/ሮ ጃማነሽ ወ/ሚካኤል፣ ቀደም ሲል የከተማው ነዋሪዎች ሲጠይቋቸው የነበሩ ጥያቄዎች በከፊል ምላሽ እያገኙ ስለመሆኑ አረጋግጫለኹ ብለዋል ተብሏል። በምዕራብ አርሲ ዞን ሻሸመኔ ከተማ የደረሱት የተከበሩ ኘ/ር ቃሲም ኪሞ ፣ በወረዳው እየተሠሩ ያሉ የተለያዩ የልማት ሥራዎችን እና ኘሮጀክቶችን ከመጎብኘታቸው ባለፈ፣ የመብራት አገልግሎት ያላገኙት ቀበሌዎች፣ የአገልግሎቱ ተጠቀሚ በሚሆኑበት ሁኔታ የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ አገልግሎት ሻሸመኔ ቅርጫፍ ለችግሮቹ ዘለቂ መፍትሔ እንዲሰጥ ሲሉ አሳስበዋል ተብሏል፡፡

እንደሌሎቹ የእንደራሴዎች ምክር ቤት አባላት ኹሉ ለሕዝብ ውክልና ሥራ ወደ ጅማ የተጓዙት የተከበሩ ወ/ሮ ለጢፋ አባ ሳንቢ ፣ ከተማዋ እያስመዘገበች ላለው ፈጣን እድገት የከተማው ነዋሪዎች ተሳትፎ ጉልህ መሆኑን መጥቀሳቸው ሲዘገብ፤ ወደዚያው ከተማ ዴዶ ወረዳ የደረሱት የተከበሩ የተከበሩ ወ/ሮ አይሻ ሼህሺፋም፣ በወረዳው ውስጥ የሚገኘው የሼኪ ጤና ጣቢያ የአገልግሎት አሰጣጥ እየተሻሻለ መምጣቱን ተናግረዋል ተብሏል። በከተማዋ ሊሙ ኮሳ ወረዳ እና በልሙ ገነት ከተማ ነዋሪዎች ጋር የተወያዩት የተከበሩ ወ/ሮ ሙስሊማ ረሺድ በበኩላቸው፣ የማኅበረሰቡ የመልማት ፍላጎት እና እየተሰራ ያለው ሥራ እጅግ የሚበረታታ መሆኑን ጠቅሰዋል ተብሏል። በወርኃ ነሐሴ ወደ ምሥራቅ ባሌ ዞን ብቅ ያሉት የተከበሩ ወ/ሮ ሳዲያ አማን፣ በዞኑ አቅም የማይፈቱ የሕዝብ ጥያቄዎች ለሚመለከታቸው አካላት እንደሚቀርቡ ሲገልጡ፤ ወደዚያው ዞን ጊነር ወረዳ ለደረሱት የተከበሩ ወ/ሮ ፋንታዬ ለገሰ ደግሞ፣ ተወያዩ ሕዝብ የመድኃኒት እጥረት፣ የመሠረተ-ልማት ዝርጋታ እንዲሁም በአብዛኞቹ ቀበሌዎች የመብራት ተደራሽነት አለመኖር እንዲሁም የንጹሕ መጠጥ ውኃ እና የኔትዎርክ ችግሮች የሚሉት ከተነሱላቸው ጥያቄዎች መካከል ዋንኞቹ መሆናቸውን ከምክር ቤቱ ያገኘነው መረጃ ይጠቁማል። በዞኑ ወደሚገኘው በደሎ መና ወረዳ የሄዱት፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የከተማ፣ መሠረተ-ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ኘሮፌሰር ሙሐመድ አብዶ፣ በዌልመል ወንዝ መስኖ ኘሮጀክት የሚገኘው ዋናው አከፋፋይ ቦይ ዉስጥ በዝናብ ወቅት አፈር ተንሸራቶ በቀላሉ ስለሚገባ ይህንን ለመከላከል ከርክብክቡ በፊት የእርምት እርምጃ መውሰድ እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል ተብሏል።

የሕዝቡን የልማት ጥያቄዎችን በፍጥነት ለመመለስ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ቅንጅታዊ አሠራር ወሳኝ መሆኑን የገለጡት ደግሞ፣ ሻሸመኔን የጎበኙት የተከበሩ የተከበሩ አቶ ወጌ ቁፋ መሆናቸው ሲዘገብ፤ በዚያው ዞን በወተራ ሻጉሌ እና በጃሎ ወረዳዎች የውክልን ሥራቸውን የከወኑት ኘ/ር ቃስም ኪሞ፣ የመሠረተ-ልማት ተደራሽነት፣ የጤና ተቋማት የግብዓት አቅርቦት እጥረት፣ የመብራት እና የኔትወርክ ተደራሽነት፣ የመኖሪያ ቤት ችግር፣ የትምህርት ጥራት፣ የምርጥ ዘር አቅርቦት፣ የኑሮ ውድነት እና የመልካም አሥተዳደር ክፍተቶች የሚሉት ከተነሱላቸው እና እንደራሴውም ማብራሪያዎችን ከሰጡባቸው ጥያቄዎች መካከል ዋንኞቹ መሆናቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

በዚኽ የነሐሴ ዕትም ሽፋን በሰጠነው የውክልና ሥራ ከተጎበኙት የኦሮሚያ ዞኖች መካከል ቄለም ወለጋ ይገኝበታል። በዞኑ ጅማ ሆሮ እና ጋዎ ቄቤ ወረዳ ለዚኹ ግብር የሄዱት የተከበሩ ወ/ሮ ባዩሽ ብርሃኑ ፣ በወረዳዎቹ ቀበሌዎች መሰራት የነበረባቸው የመብራት ኃይል አቅርቦት ማስፋፊያ አለመሠራቱ በሕዝቡ ዘንድ ቅሬታን ማስነሳቱን አድምጠዋል ተብሏል። ምዕራብ ሐረርጌ ዞን የደረሱት የተከበሩ ነስረዲን አብዱልሙሲን በበኩላቸው፣ በዞኑ ያለውን የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሳለጥ በጤና ተቋማት የተሰሩ ኘሮጀክቶች በተጨባጭ የሚታዩ ውጤቶችን እያመጡ መሆኑን ገልፀዋል ተብሏል። ወደ ጅማ ዞን ያቀኑት የተከበሩ ወ/ሮ ለጢፋ አባተማም፣ ከዞን እና ወረዳ አመራሮች እና በኹሉም የአሥተዳደር እርከኖች እንዲሁም ከተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ጋር ውይይት ማድረጋቸው ሲዘገብ፤ ወደዚያው ዞን ጎማ ወረዳ የድረሱት የተከበሩ ሞጋ አባቡልጉ፣ ቀደም ሲል ከሕዝብ ለቀረቡ ጥያቄዎች አበረታች ምላሽ መሰጠቱን ገልጠዋል ተብሏል። በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የነገሌ አርሲ ከተማ እንደራሴዋ የተከበሩ ወ/ሮ ጃማነሽ ወ/ሚካኤል በተራቸው፣ የወከሉትን ማኅበረሰብ ካወያዩ በኃላ ለከተማ አመራሩ ግብረ-መልስ መስጠታቸውን መረጃው ያመለክታል።

በምዕራብ አርሲ ዞን በገዳብ ሀሳሳ ወረዳ ለውክልና ሥራቸው ብቅ ላሉት የተከበሩ ዶ.ር. ሩቅያ አልይ፣ ተወያዮቹ የመልካም አሥተዳደር፣ የመብራት እና የመጠጥ ውኃ ችግሮች እንዲሁም የአርዳይታ ኮሌጅ የመንገድ ጉዳይ ካነሱላቸው ጥያቄዎች ቀዳሚዎቹ ናቸው ተብሏል። የዴዶ ናዳ ገጠር መንገድ በየዓመቱ ጥገና ቢደረግለትም አገልግሎት መስጠት ባለመቻሉ ለችግሩ ዘላቂ መፍትሔ እንዲሰጣቸው ተውያዮቹ የጠየቁት ደግሞ፣ የተከበሩ ወ/ሮ ጫልቱ ሞሐመድ ሲሆን፤ በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ወንጪ የሚገኘው የምርጫ ክልል ተወካይ ለሆኑት የተከበሩ ወ/ሮ ነጋሴ ባይሳም ተመሳሳይ የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች ተነስተውላቸው እርሳቸውም ምላሽ እና ማብራሪያ ሰጥተዋል ተብሏል። መንግስት ሰላም እና ፀጥታን እንዲኹም ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ እንደሚገኝ ሲናገሩ የተደመጡት ደግሞ፣ ወደ ምዕራብ ሸዋ ዞን የሄዱት የተከበሩ ዶ.ር. ፈቃዱ መንግስቱ ነበሩ።

በዚኹ የኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን የተለያዩ ፕሮጀክቶችን እና የግብርና ልማት እንቅስቃሴዎችን የጎበኙት የተከበሩ ዲታ ኑራ፣ የምልከታው ዓላማ የሕዝቡን የልማት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በወረዳው እየተተገበሩ ያሉ የልማት ሥራዎች ያሉበትን ሁኔታ በመገምገም፣ በጥሩ ደረጃ ላይ ያሉትን ለማበረታታት እና የተጓተቱትን ደግሞ ለመደገፍ ያለመ ነው ሲሉ ተናግረዋል ተብሏል። ወደ በምስራቅ ወለጋ ለተጓዙት የተከበሩ ወ/ሮ አያንቱ ጉተታ፣ በወረዳዎቹ ባለው እምቅ አቅም ፋብሪካም ሆነ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉላቸው ተወያዮቹ ጥያቄ አንስተውላቸዋል ተብሏል። በምስራቅ ወለጋ ጅማ አርጆ ወረዳ የሚገኙትን መራጮቻቸውን ያወያዩት የተከበሩ ዶ.ር. ብዙአየሁ ደገፋ በበኩላቸው፣ የአርጆ ዲዴሳ ስኳር ፋብሪካ በቀጣይ በጀት ዓመት ሥራ ለመጀመር ዝግጅት እያጠናቀቀ መሆኑን ተናግረዋል ተብሏል። ጅማ የተገኙት የተከበሩ ወ/ሪት ፈይማ ሼ/ጀማል አባማጫ፣ ከዚህ በፊት በመራጭ-ተመራጭ መድረክ ተነስተው የነበሩ ጥያቄዎችን ለመፍታት መንግስት ሰፋፊ ሥራዎች መስራቱን ሲጠቁሙ፤ ቡኖ በደሌ ዞን የደረሱት የተከበሩ ፍቃዱ ሞሲሳ በበኩላቸው፣ በመንግስት የተሰሩ ዋና ዋና የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ፣ የፓለቲካ፣ የመሠረተ-ልማት እና የዲፕሎማሲ ስራዎችን ለመራጮቻቸው አብራርተዋል ተብሏል። በምዕራብ ሐረርጌ ዞን የመራጭ ተመራጭ ውይይት ያደረጉት የተከበሩ ጂሀር መሀመድ፣ የልማት ጥያቄዎችን ከመሰረቱ ለመመለስ ዘላቂ ሰላም አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑን ገልፀው፣ ኅብረተሰቡ ለሰላም ዘብ በመቆም መስራት እንዳለበት አሳስበዋል ተብሏል። ለምዕራብ ዞን ተወካዩ የተከበሩ ደረጀ ደበላ፣ የጤና፣ የኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ የመንገድ፣ የአፈር ማዳበርያ ዋጋ መናር እና የኑሮ ውድነት መሰል ጥያቄዎች ተነስተውላቸው እንደነበር ሲዘገብ፤ ለምሥራቅ ወለጋ ዞኗ ተወካይ የተከበሩ ወ/ሮ ኤልሳቤጥ እጅጉም፣ ይኽን መሰሎቹ የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች ከመራጮቻቸው ተነስተው እርሳቸውም ማብራሪያዎችን ሰጥተዋል ተብሏል።

በዚኹ የኦሮሚያ ክልል የሚገኘው ቡኖ በደሌ ዞንም፣ በወርኃ ነሐሴ የእንደራሴዎቹ የውክልና ሥራ ከተከናወነባቸው ዞኖች አንዱ ነበር። በዞኑ የተገኙት የተከበሩ ወ/ሮ አለምነሽ ብርሃኑ፣ ከተወያዮቹ የተነሱት ጥያቄዎች በየደረጃው በሚገኙ ሥራ አሥፈፃሚዎች ምላሽ እንዲሰጣቸው እንደሚያደርጉ መናገራቸው ሲጠቀስ፤ ወደ ምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ለተጓዙት የተከበሩ ፋህሚ አሊም፣ ተመሳሳይ የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች ቀርበውላቸው እንደነበር የምክር ቤት ዘገባ ያመለክታል። ወደ ሰሜን ሸዋ ዞን የተጓዙት የተከበሩ ወ/ሮ ፋኖስ ኃይሉ፣ ከመራጮቻቸው ጋር በሰላም እና ፀጥታ እንዲኹም በልማት እና በመልካም አሥተዳደር ዙሪያ ሲወያዩ፤ በጅማ ዞን ሸቤ ሶምቦ ወረዳ፣ አበረታች የልማት ሥራዎች እየተሠሩ ስለመሆኑ የተናገሩት ደግሞ የተከበሩ ካሊድ አባመጫ ነበሩ። የተከበሩ ወ/ሮ ፅጌ ደንቦባም፣ የሱሉልታ ወረዳን መራጮቹ ሲያወያዩ፤ የተከበሩ ሲ/ር አሚራ መሃመድ በምዕራብ ሐረርጌ ዞን የአዳቡልቱ እና ዴሳ ከተማ መራጮችን፣ የተከበሩ ወ/ሮ አረጋሽ ተክሌ በበኩላቸው የበዴሳ ከተማ ነዋሪዎችን በመልካም አሥተዳደር፣ በዲሞክራሲያዊ ጥያቄዎች እና በመሠረተ-ልማት ጉዳዮች ላይ አወያይተዋል ተብሏል።

ኢሉባቦር ዞን የደረሱት የተከበሩ ወ/ሮ እታገኝ እሸቱ፣ በልማት፣ በመልካም አሥተዳደር እና በመሠረተ-ልማት ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የመራጭ ተመራጭ ውይይት ማካሄዳቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ሲያመለክት፤ የተከበሩ አሜ አብደላ በተራቸው፣ በምዕራብ ሐረርጌ ዞን ምጫታ ምርጫ ክልል ሀዊ ጉዲና ወረዳ ተገኝተው መራጮቻቸው ባነሷቸው ጉዳዮች ላይ አንድ የውይይት መድረክ መርተዋል ተብሏል።

## ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል . . .

በወርኃ ነሐሴ፣ እንደራሴዎቹ ሕገ-መንግሥታዊ የውክልና ሥራቸውን ከከወኑባቸው ክልሎች መካከል ሌላይኛው የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ነበር። በዚኹ ወር መጀመሪያ ወደዚያ ክልል ያመሩት የተከበሩ መለሰ መና፣ የክልሉ መንግስት ሕዝቡ ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት የሚያደርገውን ሁለንተናዊ ጥረት አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ሲሉ አስገንዝበዋል ተብሏል። በእንደራሴዎች ምክር ቤት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው በወላይታ ዞንም ተገኝተው፣ በተለያዩ አካባቢዎች ችግኝ በመትከል ረገድ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች የሚደነቁ መሆኑን በመጥቀስ፣ ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል ሲሉም ተናግረዋል። በክልሉ ወደሚገኘው ሳውላ ከተማ ያመሩት የተከበሩ ወ/ሮ ትዕግስት ታደለ፣ በጎፋ ዞን በኹሉም አካባቢዎች የተነሱ የልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎችን በዝርዝር ለዞኑ አሥተዳደር ምክር ቤት ማቅረባቸው ሲሰማ፤ የተከበሩ አቶ ጋሸያለው ገላው በበኩላቸው፣ ከበቶ ከተማ መራጮቻቸው ጋር ተወያይተዋል ተብሏል። ወደ በኧሌ ዞን ኮላንጎ ዙሪያ ወረዳ የሄዱት የተከበሩ ማታማ ማካ፣ ከአካባቢው ማኅበረሰብ ጋራ የውይይት መድረክ እንደነበራቸው የምክር ቤቱ ዘገባ ሲጠቁም፤ በጎርካ ወረዳ ሻፋሌ ቀበሌ የደረሱት የተከበሩ ዶ.ር. አወቀ አምዛዬ በበኩላቸው፣ ከተወያዮቹ የተነሱት ጥያቄዎች በየደረጃው ያሉ የወረዳ እና የዞን አመራሮች ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው አሳስበዋል ተብሏል። በዚኹ ደቡብ ክልል ወደሚገኘው ኮሬ ዞን ኬሌ ከተማ፣ ለመሰል ሕገ-መንግሥታዊ የውክልና ተግባራቸው ብቅ ያሉት፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የጽሕፈት ቤት ኃላፊ ተወካዩ ከረዩ ባናታ፣ የበጎ አድራጎት ሥራ ለመሥራት ዕድሜ፣ ጾታ፣ ብሔር አልያም ሃይማኖት እንደማይጠይቅ ገልጸዋል ተብሏል። ወደ ደቡብ ኦሞ ዞን የደረሱት የተከበሩ አቅናው ካውዛ፣ ሕዝቡ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ደረጃ በደረጃ ምላሽ እንዲያገኙ መንግስት ትኩረት እንደሚያደርግ ሲያስገነዝቡ፤ የተከበሩ አቶ እሸቱ ገ/ማርያም በበኩላቸው፣ በማጂ ወረዳ የመራጭ ተመራጭ ውይይት አድርገዋል ተብሏል። ከደቡብ ኦሞ ዞን ሕዝብ ለተነሱ የልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች ግብረ-መልስ የሰጡት የተከበሩ አጉ ደባን መሆናቸው ሲዘገብ፤ የተከበሩ አቶ ጋሻያለው ገላ በበኩላቸው፣ በቀደመው ውይይት በሕዝቡ የተነሱ ጥያቄዎችን መነሻ በማድረግ የተመለሱ ጉዳዮችን እና በቀጣይ ከሕዝቡ ጋር በሚደረጉ የውይይት ነጥቦች ላይ ገለፃ አድርገዋል ተብሏል።

በዲላ የቡሌ ምርጫ ተወካዩ የተከበሩ ግዛቸው አየለ፣ መንግስት የሕዝብን የልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎችን ለመመለስ በቁርጠኝነት ሊሰራ ይገባል ሲሉ፤ በኅብረተሰቡ ዘንድ ጥያቄ የነበረው የጌዴኦ ቴሌቪዥን ጥያቄ ምላሽ በማግኘቱ የመድረኩ ተወያዮች መግለፃቸው የተሰማው ደግሞ፣ የተከበሩ ዶ.ር. ኢንጂነር ስለሽ ኮሬ ናቸው ተብሏል።

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ኣሪ ዞን በተካሄደው የመራጭ-ተመራጭ መድረክ የተገኙት የተከበሩ ኢንጂነር አብዮት ደለለኝ፣ በ2018 ዓ.ም. በጀት ዓመት ለመፈጸም የእቅድ አካል የተደረጉትን አበይት ተግባራት አቅርበዋል ተብሏል። የተከበሩ ወ/ሮ ምትክነሽ ጨለቀ፣ ከዳራማሎ ወረዳ እና የዋጫ ከተማ መራጮቻቸው ጋር መወያየታቸው ሲዘገብ፤ የዲታ ወረዳ ተወካዩ የተከበሩ ዶ.ር. አዳነ አልቶም፣ የአገሪቱ ሕገ-መንግሥት ፓርላሜንታዊ ሥርዓትን የሚከተል በመሆኑ ሕግ አውጪው፣ ሕግ አሥፈጻሚው እና ሕግ ተርጓሚው ተለይተው ሚናቸውን እየተወጡ እንደሚገኙ ለአካባቢው ሕዝብ አስረድተዋል ተብሏል። ወደ ቡርጂ የተጓዙት የተከበሩ ከድር አደም፣ ከሕዝብ የተነሱ የሰላም፣ የልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎችን በውይይት መድረኩ ላይ ሲያቀርቡ፤ የተከበሩ ወ/ሮ ፀሀይ በቀለ በተራቸው፣ ሕዝቡ የሚያነሳቸውን የልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎችን ደረጃ በደረጃ ለመመለስ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል ተብሏል። ለተከታታይ ዓመታት ከወከለን ሕዝብ ጋር በሰላም እና በፀጥታ፣ በልማት፣ በማኅበራዊ እና በመልካም አሥተደደር ጉዳዮች ዙርያ እየተወያየን ቆይተናል ሲሉ የተደመጡት ደግሞ የተከበሩ ወ/ሮ ክብነሽ ሽፈራው ሲሆኑ፤ የተከበሩ እንዳልካቸው አስራት በበኩላቸው፣ የሚታዩ የልማት እና የመልካም አሥተዳዳር ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ ማግኘት እንዲችሉ ከወከሉት ሕዝብ ጋር ተወያይተዋል ተብሏል። ከመሎ ኮዛ ወረዳ እና ከላሃ ከተማ ነዋሪዎች ጋር የተወያዩት የተከበሩ ወ/ሮ ትዕግሥት ታደለ እንደነበሩ የምክር ቤቱ መረጃ ሲጠቁም፤ በወላይታ ዞን ዳሞት ለውክልና ሥራ የተገኙት የተከበሩ ወ/ሮ መቅደስ ደስታ፣ ከወረዳው አስተባባሪዎች ጋር በመሆን በወረዳው የተሠሩ እና እየተሠሩ የሚገኙ የልማት ሥራዎችን ጎብኝተዋል ተብሏል።

የኢፌዴሪ የእንደራሴዎች ምክር ቤት አባል የተከበሩ ወ/ሮ እታፈራሁ ሞታ፣ በክልሉ የሚገኘውን አዴ ሻንቶ ጤና ጣቢያን መጎብኘታቸውን ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ሲያመለክት፤ ወደ ይርጋጨፌ የሄዱት የተከበሩ ወ/ሮ ክብነሽ ሽፈራው፣ ሕዝቡ የሚያነሳቸው እና በወቅቱ ምላሽ ያላገኙ የልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች እንዲፈቱ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር ውይይት የሚደረግ መሆኑን ለመራጮቻቸው ነግረዋቸዋል ተብሏል። የሐመር ወረዳ እንደራሴዋ የተከበሩ ሲስተር ጎይቲ ዋንጮ፣ በኤሪያ ቃይሳ ቀበሌ እየተሰሩ ያሉ የልማት ሥራዎችን ጎብኝተው፣ በአከባቢው በሚሰሩ የልማት ሥራዎች ላይ ኅብረተሰቡ በባለቤትነት የነቃ ተሳትፎ ማድረግ እንዳለበት ማሳሰባቸውን ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ያሳያል።

## ድሬ ዳዋ ምን ጉዳዮች አሳሰቡኝ አለች?




የተከበሩ ዶ.ር. ቢፍቱ መሐመድ በውክልና ሥራቸው ላይ፣

በወርኃ ነሐሴ ወደ የከተማ አሥተዳደሯ ድሬ ዳዋ የተጓዙት የተከበሩ ዶ.ር. ቢፍቱ መሐመድ፣ በቀጣይ የሚነሱ የልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ ሕዝቡ ለሰላም ቅድሚያ መስጠት እንዳለበት ጠቁመው የሚመለከታቸው አካላት በየደረጃው ኃላፊነት በመውሰድ ሊሰሩ እንደሚገባ አሳስበዋል ተብሏል። ሌላይኛው የከተማይቱ እንደራሴ የተከበሩ አብዱልጂዋድ መሀመድ፣ ማኅበረሰቡ በባለፉት ጊዜያት ተነስተው የነበሩ ጥያቄዎች የተመለሱትን በማድነቅ እና በማመስገን፣ የአገሪቱን የልማት ጥያቄ የመመለስ አቅም በተረዳ መልኩ የተነሱ ጥያቄዎች ተገቢ መሆናቸውን መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ያመለክታል። የቀለዐድ ክላስተር ማኅበረሰቦች፣ በመሠረተ-ልማት አውታር ዝርጋታ በተለይም ከመጠጥ ውኃ እና ከመስኖ ውኃ አቅርቦት ጋር በተያያዘ ያሉባቸውን ችግሮች ያነሱበትን ውይይት መምራታቸው የተዘገበው የተከበሩ ዶ.ር. ቢፍቱ መሀመድ ነበሩ ተብሏል።

## ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያስ ምን ተነስቶ ነበርን?



በከፋ ዞን በጭሪ መደበኛ ምርጫ ክልል ዴቻ ወረዳ በበሃ ክላስተር ተወካይ የተከበሩ ወ/ሮ አለምነሽ ገ/ማርያም ከአካባቢው አስተዳደር አላካት ጋር በመሆን ማህበረሰቡን ሲያወያዩ፡፡

በዚኹች የእንደራሴ ዕትም ሽፋን በሰጠነው የነሐሴ ወር የውክልና ሥራ በተካተተው ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፣ እንደራሴዎች እና የክልሉ ምክር ቤት አባላት የመራጭ ተመራጭ ውይይት በመሩበት ወቅት በመድረኩ የተገኙት የተከበሩ ዳውድ መሀመድ፣ ባለፈው ጊዜ ከመራጩ ሕዝብ ጋር በተፈጠረው መድረክ የተነሱ የልማት ጥያቄዎችን በሚመለከት ከአሥፈጻሚ ተቋማት ጋር ተገቢው መግባባት ላይ መደረሱን መናገራቸው ተዘግቧል። በይሁንታ ድምጹን ሰጥቶ ከመረጠው ሕዝብ ጋር በቅርበት መምከር አገርን ያሻግራል ሲሉ የተደመጡት ደግሞ፣ ሸኪበዶ እና ጎጃ ቀበሌዎች የተገኙት የተከበሩ አዝመራ አንደሞ ሲሆኑ፤ ሌላይኛዋ እንደራሴ የተከበሩ ወይዘሮ ፋናዬ መለሰ፣ የብልጽግና ፓርቲ አገረ-መንግሥት ግንባታ ላይ የበኩሉን ሚና እየተወጣ በመሆኑ፣ ወጣቶቹ በኹሉም ዘርፎች ግንባር ቀደም መሆና አለባቸው ብለዋል ተብሏል። ወደ ካፋ ዞን ብቅ ያሉት የተከበሩ ወ/ሮ አለምነሽ ገ/ማርያም፣ ሕዝቡ በተደጋጋሚ የሚያነሳቸው እና በወቅቱ ምላሽ ያላገኙ የልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች እንዲፈቱ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር ውይይት የሚደረግ መሆኑን አስገንዝበዋል። በኢፌዴሪ የእንደራሴዎች ምክር ቤት የመኽን ተወካዩ የተከበሩ ፋቃዱ ባድልባ፣ ሕዝቡ የሚያነሳቸው የመሠረተ ልማት ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ እንዲያገኙ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር እንደሚሠራ ማሳሰባቸው ሲዘገብ፤ የተከበሩ ወ/ሮ አረጋሽ ክፍሌ በበኩላቸው፣ በመኤኒት ጎልዲያ ወረዳ በርካታ የመሠረተ-ልማት ጥያቄዎች ምላሽ እንዳገኙ አንስተው፣ ያልተከናወኑት ቀሪ የመሠረተ-ልማት ሥራዎች ምላሽ እንዲያገኙ በጋራ እንደሚሰራ ገልፀዋል ተብሏል። የተከበሩ እሸቱ ገ/ማሪያምም፣ በማጂ ወረዳ እየተገነቡ የሚገኙ የጸሐይ ኃይል አመንጪ ፕሮጀክቶች ላይ ምልከታ ካደረጉ በኋላ፣ ማኅበረሰቡ ለበርካታ ዐሥርታት ብርሃን እየናፈቀ የኖረ ሕዝብ መሆኑን ጠቅሰው፣ ለፕሮጀክቱ እንቅፋት የሚሆኑ በአካባቢውም ሆነ በክልሉ የተፈጠሩ ተግዳሮቶች እንዲፈቱ በየደረጃው ካለው የመንግስት አካል ጋር የሚነጋገሩ መሆኑን አንስተዋል።

በዚኹ ክልል ወደሚገኘው ሸኮ ከተማ ለመሰል ሕገ-መንግሥታዊ ተግባራቸው የደረሱት የተከበሩ ወ/ሮ ዘሙ ተስፋዬ፣ በውይይቱ ተሳታፊዎች የተነሱት ጥያቄዎች ተገቢ ምላሾችን ማግኘት እንዲችሉ ለአሥፈጻሚ አካላት በየዘርፉ እንደሚያቀርቡ የምክር ቤቱ መረጃ ሲያመለክት፤ የካካ ምርጫ ክልል ተወካዮ የተከበሩ ወ/ሮ ፋናዬ መለሠ፣ በወረዳው ከሚገኙ 13 ቀበሌዎች ከተውጣጡ የማኅበረሰብ ተወካዮች ጋር በልማት እና በመልካም አሥተዳደር ዙሪያ ውይይት አድርገዋል ተብሏል። እንደራሴዎች የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመፈፀም በሕዝቡ የሚነሱ ጥያቄዎችን ወርዶ መስማት እንደሚያስፈልጋቸው መናገራቸው የተዘገበው ደግሞ የተከበሩ ቆጭቶ ገ/የሱስ ሲሆኑ፤ የተከበሩ ወ/ሮ እየሩሳሌም ሌዊ በበኩላቸው፣ የኮሪደር ልማት ሥራዎችን በተመለከተ ከመንግስት በተጨማሪ ማኅበረሰቡ ከኪሱ በማዋጣት እና ይዞታውን በመልቀቅ በፍጥነት እየተሰራ መሆኑ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ብለዋል ተብሏል።



በዳውሮ ዞን ኢሠራ ወረዳ የኢሠራ ቶጫ ምርጫ ክልል ተወካይና የፓርላማ አባሉ የተከበሩ አቶ ተስፋዬ ባንጉ ከወከላቸው ሕዝብ ጋር በተወያዩበት ወቅት

በክልሉ ወደሚገኘው ገሣ ጫሬ ከተማ ለደረሱት የተከበሩ ወ/ሮ አስቴር ከፍታው፣ የንጹሕ መጠጥ ውኃ ተሰርቶ ባለመጠናቀቁ ምክንያት መላው የከተማው ነዋሪዎች ችግር ላይ ወድቀዋል ሲሉ ተሳታፊዎቹ ሲያነሱላቸው፤ ወደ ዳውሮ ዞን ብቅ ያሉት የተከበሩ ተስፋዬ ባንጉ፣ ከመራጮቻቸው ጋር ውይይት ባደረጉበት ወቅት፣ በፌደራል መንግሥት በዕቅድ የተያዙ እና በምክር ቤቱም የፀደቁ በተለይም የመንገድ መሠረተ-ልማት ዕቅድ እና መነሻ በጀትም መያዛቸውን አብራርተዋል ተብሏል። በዚያው ክልል ወደሚገኘው ኮንታ የተጓዙት የተከበሩ ኢያሱ ሳላ፣ በተለያዩ ጊዜያት ከሕዝቡ የተነሱ የልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች ደረጃ በደረጃ እየተመለሱ መምጣታቸውን ማንሳታቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ሲጠቅሳቸው፤ የሱሪ ሕዝብ ተወካዮ የተከበሩ ወ/ሪት ትደነቅ ጉልዱ፣ በመልካም አሥተዳደር እና በልማት ሥራዎች ዙሪያ ከቀበሌው ከተወጣጡ የምክር ቤት አባላት እና ከወረዳው አመራሮች ጋር ውይይት አካሂደዋል ተብሏል።

## በሲዳማ መድረኮችስ ምን ተነሳ?



የኢፌድሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የተከበሩ ወ/ሮ አለሚቱ አበበ በሲዳማ ክልል በደቡባዊ ሲዳማ ዞን ደራ ምርጫ ክልል የወከላቸውን ሕዝብ ሰብስበው ባወያዩበት ወቅት

በወርኃ ነሐሴ፣ እንደቀደሙት ክልሎች ኹሉ የተለያዩ የልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች በተነሱባት ሲዳማ ክልል የተገኙት የተከበሩ ወ/ሮ አለሚቱ አበበ፣ ከመሠረተ-ልማት ፍትሓዊነት እና ተደራሽነት አኳያ በግብርናው ዘርፍ ምርታማነትን በማሳደግ የምግብ ዋስትና ከማረጋጥ አንፃር ያሉ ችግሮች እና የመፍትሔ አቅጣጫዎችን እንዲኹም መልካም አጋጣሚዎችን አስመልክቶ ከመራጮቻቸው ጋር ሰፊ ውይይት ማድረጋቸው ተዘግቧል። በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት አባል እና የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ሰለሞን ላሌ፣ ሕዝቡ ያነሳቸው ጥያቄዎች ምላሽ ማግኘታቸው መንግስት የሕዝብን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እየተጋ ያለ መሆኑን ማሳያ ነው ብለዋል ተብሏል። ሌላይኛዋ የሲዳማ እንደራሴ ወ/ሮ መሰረት ማሞም፣ ከመራጮቻቸው ጋር በሰላም፣ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ፣ በመሠረተ-ልማት እና በመልካም አሥተዳደር ጉዳዮች ዙሪያ መወያየታቸውን ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ይጠቁማል። ወደ አለታ ወንዶ ከተማ ብቅ ያሉት የተከበሩ ወ/ሮ መሰለች ካዊሶ፣ አዳዲስ የተከፈቱ የመንገድ ሥራዎች፣ የኮብልስቶን ንጣፍ ሥራ፣ የከተማውን ስታዲየም ግንባታ እንዲኹም አዲስ የተገነባው ጤና ጣቢያ ሥራ ያለበትን ደረጃ ሲመለከቱ፤ የተከበሩ ዶ.ር. ሰላማዊት መንገሻም፣ በዚያው ከተማ ከተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ከተወጣጡ ነዋሪዎች ጋር ውይይት አድርገዋል ተብሏል።

## ወደ የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል. . .



የተከበሩ ወ/ሮ አያን አሊ በሺኒሌ ዞን ከሕዝቡ ለተነሱት የልማት ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ከዞን እና ከወረዳው አመራር ውይይት ባደረጉበት ወቅት

በምሥራቁ የኢትዮጵያ ክፍል የሚገኘው የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል፣ በዚኹ ሸፋን በሰጠነው ወር ኹለት እንደራሴዎቹን ማስተናገዱን የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት መረጃ ያመለክታል። ሸበሌ ዞን የደረሱት የተከበሩ ፋይሳል ኦዶዋ፣ 100 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለውን እና በጎዴ እና ሃርጌሌ መካከል ያለውን የመንገድ ግንባታ ሲጎበኙ፤ ሺኒሌ ዞን የሄዱት የተከበሩ ወ/ሮ አያን አሊ በበኩላቸው፣ ከሕዝቡ ለተነሱት የልማት ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መነጋገራቸውን ገልፀዋል ተብሏል።

## ከአፋር በኩልስ. . .



የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የተከበሩ አቶ አብዱ ሀሰን በአፋር ክልል በመንገድ ፕሮጀክት ግንባታ ዙሪያ ከፕሮጀክቱ የስራ ሃላፊዎች ጋር ውይይት ባደረጉበት ወቅት

ክረምቱን ወደ አፋር ክልል ከደረሱት የኢትዮጵያ እንደራሴዎች መካከል ቀዳሚዋ ወደ አርጎባ ልዩ ወረዳ የተጓዙት የተከበሩ ወ/ሮ ፋጡማ አሊ ኢብራሂም፣ በባለፈው በጀት ዓመት ከኅብረተሰቡ እና ከመሥተዳደር ምክር ቤቱ ከተነሱ ጥያቄዎች ውስጥ በዋነኝነት የጋቺኒ ከተማ የስልክ ኔትወርክ እና ከማዳበሪያ ጋር ተያይዘው የተነሱ ጥያቄዎች በተወሰነ ደረጃ የተመለሱ መሆኑን ገልፀዋል ተብሏል በተጨማሪም የተከበሩ ወ/ሮ ፋጡማ አሊ፣ ሕዝቡ ያነሳቸው የልማት፣ የመልካም አሥተዳደር እና የማኅበራዊ አገልግሎት፣ እንዲኹም የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ በየደረጃው ለሚገኙ አሥፈፃሚ አካላት እንደሚያቀርቡ ቃል ገብተዋል። ሌላይኛው እንደራሴ የተከበሩ አብዱ ሀሰን፣ በክልሉ በሚካሄደው የመንገድ ፕሮጀክት ግንባታ ዙሪያ ከፕሮጀክቱ የሥራ ኃላፊዎች ጋር ውይይት ማድረጋቸውም ተዘግቧል።

## አዲስ አበባውያንስ ምን አሉ?



በአዲስ አበባ አራዳ ክፍለ ከተማ የመራጭ ተመራጭ መድረክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የተከበሩ ፕ/ር እያሱ ኤሊያስ እና የተከበሩ ዶ.ር. ብርሀነ መስቀል ጠና የክፍለ ከተማው ተመራጮችና አመራሮች ጋር ባካሄዱበት ወቅት

ከድሬ ዳዋ በመለስ፣ ኹለተኛዋ አሥተዳደራዊ ከተማ አዲስ አበባም፣ በወርኃ ነሐሴ የሕዝብ ውክልና ሥራዎች ተከናውኖባታል። ወደ ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ-ከተማ ብቅ ያሉት የሰላም ሚኒስቴር ሚንስትር ዴኤታው የተከበሩ ዶ.ር. ኸይረዲን ተዘራ፣ መንግሥት እና ሕዝብ በትብብር በየደረጃው ያከናወኗቸው ኘሮጀክቶች የዜጎችን ሕይወት ለማሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል ሲሉ ተደምጠዋል። ወደ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ-ከተማ የደረሱት የተከበሩ ረዳት ኘ/ር እንዳልካቸው ሌሊሳ፣ ነዋሪዎች የተሰሩ የመሠረተ-ልማት ሥራዎችን የመጠበቅ እና የአካባቢውን ሰላም ከፀጥታ አካላት ጋር በመቀናጀት ሊያስጠብቁ እና ከአስተዳደሩ ጋር በጋራ ሊሰሩ እንደሚገባ ጠቁመዋል ተብሏል። የግብርና ሚኒስትር ሚንስቴር ዴኤታው የተከበሩ ኘ/ር እያሱ ኤሊያስ፣ ከዚህ በፊት በሕዝቡ የተነሱ የመልካም አሥተዳደር፣ የአገልግሎት አሰጣጥ እና የልማት ጥያቄዎች ምላሽ በማግኘታቸው አሥተዳደሩን ማመስገናቸው ሲጠቀስ፤ የኮተቤ ዩኒቨርሲቲው ኘሬዝደንት የተከበሩ ዶ.ር. ብርሃነ መስቀል ጠና በበኩላቸው፣ የ 2017 በጀት ዓመት አስተዳደሩ በሕዝቡ የተነሱ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ በበሳል አመራር ሰጭነትና በተሻለ ተነሳሽነት በትኩረት እየሰሩ መሆናቸውን ገልጸዋል ተብሏል። ወደ ዋና ከተማዋ ልደታ ክፍለ-ከተማ የሄዱት የተከበሩ ወ/ሮ ሙሉ ይርጋ፣ በማኅበረሰብ የተነሱ የልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎችን ለመፍታት በጀት ተበጅቶ ደረጃ በደረጃ የተሰሩ ሥራዎች እንዳሉ በማንሳት በፌደራል፣ በከተማ እና በክፍለ-ከተማ ደረጃ ችግሮችን ለይቶ መፍታት መቻሉን ገልፀዋል ተብሏል።

## ስለ ቤኒ ሻንጉል ጉምዝስ በክረምቱ ምን ተሰማ?





በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሕዝብ ተወካይ የሆኑት የተከበሩ ወ/ሮ መናሂል ኢምራን በአቡራሞ ወረዳ ከሸርቆሌ አሆፌንዲ ቀበሌ ማዕከል ነዋሪዎች ጋር በሰላም ፣ በመልካም አስተዳደርና በልማት ሥራዎች ዙሪያ በተወያዩበት ወቅት

ወደዚኽ ድንበርተኛ ክልል የተጓዙት፣ በእንደራሴዎች ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ም/ሰብሳቢው የተከበሩ ሙባረክ ኤልያስ፣ ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር በልማት እና በመልካም አሥተዳደር ጉዳዮች ዙሪያ መምከራቸውን የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ውክልና ተኮር መረጃ ይጠቁማል። በክልሉ ወደሚገኘው አቡራሞ ወረዳ የደረሱት የተከበሩ ወ/ሮ መናሂል ኢምራን፣ ከመራጮቻቸው የተነሱ የልማት ጥያቄዎች አስፈላጊ እና ተገቢ በመሆናቸው በወረዳ እና በክልል ደረጃ ባሉ አሥፈፃሚ አካላት ፈጣን ምላሽ እንዲያገኙ ይሰራል ማለታቸው ሲጠቀስ፤ ከሰዳል ወረዳ ሕዝብ ጋር የመራጭ ተመራጭ የውይይት መድረካቸውን በዲዛ ከተማ ያካሄዱት የተከበሩ ወ/ሮ ፀዳለ አበራ ነበሩ ተብሏል። በመራጩ ሕዝብ የተነሱ የልማት ኣና የመልካም አሥተዳድር ጥያቄዎች በወረዳ፣ በክልል እና በፌዴራል መንግሥት ደረጃ ምላሽ እንዲያገኙ በትኩረት እንደሚሠራ ሲናገሩ የተሰሙት ደግሞ የተከበሩ ዶ.ር. መኮንን ጎላሳ ሲሆኑ፤ ዲዴሳ ወረዳ የደረሱት የተከበሩ ዶ.ር. አብድሰመድ ሁሴን፣ የተጀመሩ የልማት ሥራዎችን በማስቀጠል እና ከኅብረተሰቡ የተነሱ የልማት ጥያቄዎች ደረጃ በደረጃ እንዲመለሱ የበኩላቸውን ድርሻ እንደሚወጡ ገልፀዋል ተብሏል።


## የውክልና ሥራ በጂዳ እና በመካ

የወሩን የባሕር ማዶ ብቸኛ የውክልና ሥራ የከወኑት የተከበሩ ዶ.ር. አብድሰመድ ሁሴን እንደነበሩ የምክር ቤቱ መረጃ ያሳያል። ከጂዳ እና መካ ማኅበረሰብ እና ከጣይፈ ሸነን ግቤ ማኅበረሰብ አባላት ጋር የተወያዩት እንደራሴው ዶ.ር. አብድሰመድ፣ የጂዳ እና መካ ማኅበረሰብ በታላቁ የሕዳሴ ግድብ ዙሪያ ላከናወነው የዲኘሎማሲ ሥራ እና ለግድቡ ግንባታ ላበረከተው የገንዘብ አስተዋጽኦ አመስግነዋል ተብሏል። በውይይቱ መገባደጃም፣ እንደራሴው ለአገራቸው እያደረጉ ላሉት በጎ አሰተዋጽኦ የአርዓያነት ሽልማት ከውይይቱ ታዳሚዎች

# የፓርላማ ዲፕሎማሲ

የ

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች በወርኃ ነሐሴ፣ ምንም እንኳን በዋናነት እንዱ ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነታቸው የሆነውን የሕዝብ ውክልና ሥራ ሲከውኑ ቢባጁም፣ ከውክልና ሥራው በመለስ ሠሥት ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ሥራዎችን ተግብረዋል።




የተከበሩ ፈትሂ ማህዲ (ዶ/ር) የውጭ ግንኙነትና ሠላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ፣
የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ሚንስትር ክቡር አለሙ ስሜ (ዶ/ር)
እና በፓኪስታን የኢፌዲሪ አምባሳደር ምባሳደር ጀማል በከር (ዶ/ር) በቱርክሜኒስታን

በዚኽ ወር ቀዳሚው የእንደራሴዎቹ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ፣ በተባበሩት መንግሥታት አዘጋጅነት ቱርክሜኒስታን አዋዛ ከተማ ውስጥ በተካሄደው፣ የባሕር በር የሌላቸው ታዳጊ አገራት ጉባኤ ላይ የተደረገው ተሳትፎ ነበር። በዚያ ዓለም ዓቀፍ መድረክ ላይ የተገኘው የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን፣ ከቱርክሜኒስታኑ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ተወያይቷል ተብሏል። እንደ ምክር ቤቱ ዘገባም፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና የሠላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ፈትሂ ማህዲ፣ የባሕር በር የሌላቸው አገራት በመልክዓ-ምድራዊ አቀማመጣቸው ምክንያት ለተለያዩ ዘርፈ ብዙ ችግሮች መጋለጣቸው አግባብነት የሌለው መሆኑን አንስተው፣ ጉባኤው ተጨባጭ መፍትሔ ያመጣል ብለው እንደሚጠብቁ ሲናገሩ ተደምጠዋል። ጉባኤው ይኽንን ለመቀየር “የአዋዛ የድርጊት መርሃ-ግብር” የተሰኘ ስልት ማዘጋጀቱን ያነሱት ዶ.ር. ፈትሂ፣ የድርጊት መርሃ ግብሩን አገራት በአግባቡ ከተገበሩት ከባሕር በር ጋር በተያያዘ ችግሮችን ለመፍታት እና ተጨባጭ ውጤት ማምጣት ይችላል ብለዋል ተብሏል።

በዚያው ጉባኤ ላይ የታደሙት የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ሚንስትሩ የተከበሩ ዶ.ር. አለሙ ስሜ በበኩላቸው፣ የባሕር በር የሌላቸው አገራት የመሠረተ-ልማት ዝርጋታ እና ዘመናዊ የንግድ ኮሪደሮችን መፍጠር እና ማስፋፋት ላይ መዋዕለ-ንዋያቸውን ለማፍሰስ በትብብር መስራት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል። የቱርክሜኒስታን የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤዋ ዲ. ጉልማኖቫ በተራቸው፣ የእንደራሴዎች ምክር ቤቶች የባሕር በር የሌላቸው አገራት የልማት ዕቅዶችን ወደ ሕግ ማዕቀፍ እና ተግባራዊ እርምጃዎች በመቀየር ረገድ ወሳኝ ሚና እንዳላቸው መግለጣቸውን ከምክር ቤቱ ያገኘነው መረጃ ጠቅሷቸዋል።

የወሩ ኹለተኛው ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ የተከወነው፣ በምክር ቤቱ የውጭ ግንኙነት እና ሰላም ጉዳዮች እና የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ ከቻይና የሰብዓዊ መብቶች ኅብረተሰብ ጥናት እና ከቻይና ሕዝብ መማክርት ጉባኤ ከተውጣጣው ልዑካን ቡድን ያካሄዱት ውይይት እንደነበር ተጠቅሷል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎ፣ ኢትዮጵያ በምታከናውናቸው የልማት፣ የሰብዓዊ መብቶች እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የቻይና መንግሥት ድጋፍ እና አጋርነት በማሳየት ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል፤ ሰብሳቢው አክለውም፣ ኢትዮጵያ ሰፊ የባህል፣ የታሪክ፣ የሃይማኖት ብዝኃነት ያለባት አገር በመሆኗ ኹሉን አሳታፊ እና ፍትሓዊ ሥርዓት ለመፍጠር አገራዊ ምክክር በማድረግ ላይ እንደምትገኝ ገልጠዋል ተብሏል። የቻይናው ልዑክ ሰብሳቢው የተከበሩ ጂያንግ ጂያንጉኦ በበኩላቸው፣ ቻይና ኢትዮጵያን በአፍሪካ ተመራጭ የዲፕሎማሲ አጋር አድርጋ ትመለከታታለች ማለታቸውን ዘገባዎቹ ጠቅሰዋቸዋል።



የውጪ ግንኙነት እና ሰላም ጉዳዮችና የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ከቻይና የሰብዓዊ መብቶች ኅብረተሰብ ጥናትና ከቻይና ሕዝብ መማክርት ጉባኤ ከተውጣጡ ልዑካን ጋር

በኢፌዲሪ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ነገሬ ሌንጮ፣ ኦስትሪያ ለኢትዮጵያ ልማት የገንዘብ ድጋፍ ከሚያደርጉ የአውሮፓ ኅብረት አገራት መካከል ቀዳሚውን ስፍራ እንደምትይዝ የተናገሩበት ደግሞ፣ ሦሥተኛው የወርኃ ነሐሴ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ክንውን ነበር። ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ እና በፖለቲካው መስክ ሽግግር እያደረገች መሆኑን ጨምረው የጠቀሱት ዶ.ር. ነገሬ፣ ኦስትሪያ በትምህርት እና በጤናው መስክ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከተች ነው ብለዋል ተብሏል። ሌላይኛው የመድረኩ ተሳታፊ የተከበሩ ዶ.ር. ፈትሂ ማህዲ በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያ በቀጠናው ሰላም እንዲሰፍን በአፍሪካ ኅብረት እና በኢጋድ አማካኝነት ከፍተኛ ጥረት እያደረገች መሆኗን ገልፀው፣ በአገር ውስጥ የነበረውን ግጭት በስምምነት በመፍታት እና ሰላም እንዲሰፍን የምክክር ኮሚሽን ተቋቁሞ ጠንካራ ሥራዎች እየተሰሩ መሆኑን መጥቀሳቸው ተሰምቷል።



የውጭ ግንኙነትና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እንዲሁም የሰው ሀብት ልማት፣ ስራ ስምሪትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ከኦስትሪያ የፓርላማ ልዑክ ጋር በተወያዩበት ወቅት

የኢትዮ-አውሮፓ እና የምዕራብ አውሮፓ የወዳጅነት ቡድን ሰብሳቢው የተከበሩ አምባሳደር ዲና ሙፍቲም፣ ኢትዮጵያ በሶማሊያ እና በሱዳን ብሎም በቀጠናው ሰላም እንዲሰፍን የበኩሏን ጥረት እያደረገች ትገኛለች ሲሉ ለኦስትሪያው ልዑክ ነግረዋቸዋል ተብሏል። የኦስትሪያ የእንደራሴዎች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት ኮሚቴ አባል እና ከሰሀራ በታች የእንደራሴዎች ምክር ቤት ወዳጅነት ቡድን ፕሬዝደንት የሆኑት አክሰል ካሴገር፣ ኦስትሪያ እና ኢትዮጵያ ለበርካታ ዓመታት የዘለቀ ጠንካራ ወዳጅነት ያላቸው አገራት መሆናቸውን ጠቁመው፣ የኢትዮጵያ መንግስት እያደረጋቸው ያሉ የማሻሻያ ሥራዎችን ኦስትሪያ እንደምትደግፍ ገልፀዋል ተብሏል። በዚኽ ያላበቁት አክሰል፣ ከባሕር በር አልባነት ጋር በተያያዘ አገራቸው አውስትሪያም የባሕር በር የሌላት አገር መሆኑን አስታውሰው፣ ከጎረቤት አገሮች ጋር በትብብር እየሰሩ መሆኑን ጠቁመዋል።

# የብሪጅ አጭር ዳሰሳዊ ምልከታ በእንደራሴዎቹ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ዙሪያ

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ ሊጠናቀቅ አምስት ቀናት በቀሩት ይኸን ዓመት ጨምሮ፣ ባለፉት ዐራት ዓመታት ዘርፈ ብዙ ርዕስ ጉዳዮችን ያካተቱ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲዎችን አከናውነዋል። በተለይም ባለፉት ኹለት ዓመታት፣ ታላቁን የሕዳሴ ግድብን እና ከቅርብ ወራት አንስቶ ደግሞ በኢትዮጵያ የባሕር በር ይገባኛልነት ዙሪያ የበረቱ ዲፕሎማሲያዊ ግብሮችን ሲከውኑ ሰንብተዋል።

ይኸች የእንደራሴ የነሐሴ ዕትምም፣ ለመሆኑ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ምንድር ነው? ግቡ እና አገራዊ ፋይዳውስ? እንደራሴዎቹስ ከዚኽ የተሻለ እንዳይሰሩ ምን አግዷቸው ይሆን? የሚሉትን ተያያዥ ነጥቦች እጅጉን በአጭሩ ልትዳስሰው መርጣለች።

## የፓርላማ ዲፕሎማሲ ሲሉ . . .

የፓርላማ ዲፕሎማሲ በተለይም በድህረ-ቀዝቃዛው ጦርነት ማግስት፣ በዓለም ዓቀፋዊ እና መንግሥታዊ ባልሆኑት በተለምዶ ዐራተኛው መንግሥት በሚባሉት ሀገር በቀል እና ድንበ ዘለል ተቋማት መበርከት በተስተዋለበት ሉላዊ ዘመን ብቅ ያለ የእንደራሴዎች የዲፕሎማሲ ሥርዓታዊ ክንውን ነው። ከዚያን ዘመን አንስቶም፣ የእንደራሴዎች ምክር ቤት እና እንደራሴዎቹ ‘ራሳቸው መደበኛ በሆኑ ዓለም ዓቀፍ ጉባኤዎች እና የኹለትዮሽ አገራዊ ውክልና በያዙ መድረኮች ላይ ጭምር የሚሳተፉበትን ኹነት፣ በዚኹ ስያሜ መጥራቱ ልማዳዊ ሆነ።

የፓርላማ ዲፕሎማሲ በተለምዷዊዎቹ ዲፕሎማቶች ወይም በመንግሥት ባለሥልጣናት ሳይሆን፣ በአንድ አገር የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም የበላይ ሕግ አውጭ አካል አባላት የሚከናወን የዲፕሎማሲ ዓይነት ነው። የጋራ ግቦችን ለማራመድ፣ ዓለም ዓቀፍ ፈተናዎችን በጋራ ለመፍታት እና በአገራት መካከል የተሻለ መግባባትን ለማጎልበት በተለያዩ አገሮች በሚገኙ እንደራሴዎች መካከል የአቻ ግንኙነቶችን መፍጠር፣ ሐሳብ መለዋወጥን እና የርዕሰ-መንግሥታትን ውይይት ማበረታታትንም እንደሚያካትት፣ በዚኹ ዙሪያ የተፃፉት በርከት ያሉት ጥናቶች ያወሳሉ። የፓርላማ ዲፕሎማሲ፣ ብዙውን ጊዜም በኹለትዮሽ ወይም በብዙኃን ወገን ስብሰባዎች፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጋራ ጉባኤዎች፣ በኮንፈረንሶች እና በሌሎች ይፋዊ ስብሰባዎች አማካኝነት ይከናወናል።

እነዚኽ ኹነቶች እንደራሴዎች የተሻሉ ልምዶችን እንዲጋሩ፣ የፖሊሲ ምክረ-ሐሳቦችን እንዲያዘጋጁ እና የየራሳቸውን አገራት ብሔራዊ ጥቅሞች እንዲያራምዱ ያስችላቸዋል ተብሎ ይታመናል። ከዚኽ መሰሎቹ መደበኛ ስብሰባዎች በተጨማሪ፣ መደበኛ ያልሆነ ትስስሮሾችን መፍጠር እና ኹለትዮሽ ውይይቶችን ማድረግም፣ በፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ውስጥ ትልቅ ሚና እንደሚጫወት የነገሩ ጸሓፍት ይጠቅሳሉ። ጠቅለል ባለኹኔታ ስንመለከተው፣ የፓርላማ ዲፕሎማሲ ግቦች ተብለው መዛግብቱ ከሚጠቅሷቸው መካከልም በዋናነት የሚከተሉት ይገኙበታል፦

- ዓለም አቀፍ ትብብሮችን ማጠናከር፦ የአንድ አገር እንደራሴዎች እንደ የአየር ንብረት ለውጥ ኹለንተናዊ ተጽዕኖ፣ ድኅነት፣ የሰብዓዊ መብቶች አያያዝ እና አገራት ተኮር ውጥረቶችን መፍታትን ግባቸው ያደረጉ ዓለም ዓቀፍ እና ቀጠና ተኮር ጉዳዮችን ለመፍታት አብረው ሊሰሩ ይችላሉ።
- ዲሞክራሲያዊ ዕሴቶችን መጋራት፦ እንደራሴዎች እንደ የበላይ ሕግ አውጪነታቸው እና የየአገራቸውን ሥራ አሥፈፃሚዎች የመቆጣጠር ሕገ-መንግሥታዊ ሥልጣኖቻቸው ለሕግ የበላይነት፣ ለሥርዓታዊ ግልጽነት መጎልበት እና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር መሟገት ብቻም ሳይሆን፣ ከራሳቸው አገር ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ትግበራ ያገኟቸውን ተጨባጭ ልምዶች በፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ክንውኖቻቸው አማካኝነት የመጋራት ዕድሎችን ይፈጥራሉ፤ በዚኽ አማካኝነትም ለ‘የአገሮቻቸው ዲሞክራሲ መጎልበት ሰፊ አበርክቶ ያደርጋሉ።
- በ‘የአገራቸው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር፣ ከተለያዩ ዲፕሎማሲ ክንውናቸው የሚገኟቸውን ልምዶች በመንተራስ፣ በውጭ ጉዳይ ፖሊሲው ውስጥ ቢካተቱ ይረባሉ የሚሏቸውን ዕይታዎች ለሥራ አሥፈፃሚው በፖሊሲ ግብዓትነት በማቅረብ ተቋሙን ይረዳሉ፤ በሌላ አገላለጽ፣ የውጭ ጉዳይ ዲፕሎማሲው አሟሟይ ከመሆን ባለፈ፣ የውጭ ጉዳይ የትግበራ ግድፈቶችን አራሚ የመሆን ዕድሎችን ጭምር ይፈጥራሉ።

- ድንበር ተሻጋሪ ንግዶችን እና ዓለም ዓቀፍ የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰቶችን ወደ አገራቸው ለመሳብ፣ የሚሳተፉባቸውን ጉባኤዎች እና ሌሎች ኹለትዮሽ መድረኮችን ይጠቀማሉ። በዛ ማመቻቸት: የፓርላማ አባላት በአገሮቻቸው መካከል ያለውን የንግድ እና የኢንቨስትመንት እንቅፋቶችን ለመለየትና ለመፍታት አብረው ሊሰሩ ይችላሉ።

እኒኽ ግቦች፣ የሕግ አውጭዎች ግንኙነቶችን ለመገንባት፣ የተሻሉ ልምዶችን ለመጋራት እና የጋራ ዓለም ዓቀፍ ፈተናዎችን ለመፍታት ምቹ መድረኮችንም ይሰጣሉ። በተዘዋዋሪ፣ የእንደራሴዎች ዲፕሎማሲያዊ ሚና የሚጠናከረው በሕገ-መንግሥታዊ ሥልጣኑ የሥራ አሥፈጻሚውን የውጭ ፖሊሲ ለመቆጣጠር፣ ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶችን ለማፅደቅ እና በዓለም ዓቀፍ ጉዳዮች ላይ የሕዝብ ውይይቶችን ለማካሄድ በሚያስችለው ሥልጣን መሠረት ነው። ይኽ የሕግ አውጭው አካል በመንግሥት የውጭ ግንኙነት ላይ እንደ ወሳኝ መቆጣጠሪያ ሆኖ እንዲሠራም የሚረዳ ሲሆን፤ በተመሳሳይ ጊዜም በዓለም ዓቀፍ ጉዳዮች ላይ የአገሪቷን ዕይታ ይበልጥ ከማሳየቱ ባለፈ፣ በሌሎች አገራት ተጿራዊ ዕይታ ላይም ተፅዕኖ እንዲያሳድር ያስችለዋል ተብሎ ይታመናል።

## የእንደራሴዎቹ መንገድ

አሁን በሥራ ላይ ያለው የኢፌድሪ ሕገ-መንግሥት፣ ለኢትዮጵያ እንደራሴዎች ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ እንቅስቃሴዎች ሰፊ ቦታ ስለመስጠቱ ብዙ የተባለበት ርዕሰ-ጉዳይ ነው። ከዚኽ አንፃርም፣ የኣንደራሴዎቹ ምክር ቤት የፓርላማ ዲፕሎማሲን እንደ ዋና የሥራው አካል አድርጎ በንቃት መሳተፍ ከጀመረ ሰንበትበት ብሏል። ከላይ በአጭሩ ከጠቃቀስናቸው ግቦች አኳያ፣ ይኽን መሰሎቹ በኹለትዮሽ እና በባለብዙኋን መድረኮች፣ በዚኽ ነሐሴ ወር ጭምር የተካሄደው ዲፕሎማሲ፣ የኢትዮጵያን ግንኙነቶች ከሌሎች አገሮች የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች እና ከዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር ማስተባበርን ያካተተ ሲሆን፣ በዚኽም የኢፌድሪን ይፋዊ የዲፕሎማሲ ተግባራት በኹነኛ መልኩ ደግፏል።

ከዚኽ ባለፈም፣ በሥራ አሥፈጻሚው የተደረጉ ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶችን መርምሮ ከማፅደቅ አንስቶ፣ እንደ የዓለም ዓቀፍ የፓርላማዎች ኅብረት እና የፓን-አፍሪካ ፓርላማ ከመሳሰሉ ዓለም ዓቀፍ ተቋማት ጋር በመገናኘት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሞች ከዚኽ መሰሎቹ ስምምነቶች አኳያ ይተገበሩ ዘንድ የኢትዮጵያን ድምጽ አሰምቷል፤ ለዚኽ ማሳያ ሊሆኑ የሚችሉት፣ የታላቁ ሕዳሴ ግድብ እና በወደብ ጥያቄ ዙሪያ የተከናወኑት ተግባራት ናቸው። በእነዚኽ እንቅስቃሴዎች አማካኝነትም፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቱ በዓለም ዓቀፍ መድረክ ለኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ገጽታ ድርሻውን ተወጥቷል ማለት የሚቻል ይመስለናል።

## ጠንካራ ገጾች

- የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት እንደ የዓለም ዓቀፍ የፓርላማዎች ኅብረት በመሳሰሉ ዓለም ዓቀፍ ተቋማት ውስጥ አባል መሆኑ፣ እንደራሴዎቹ ውስብስብ ዓለም ዓቀፍ እና ቀጠናዊ ፈተናዎችን ለመፍታት እና ሰላምን እና መግባባትን ለማጎልበት በዓለም ዓቀፍ ውይይቶች ላይ የኢትዮጵያን ድምጽ ማስማት ተችሏቸዋል።

- ለዚኽ መሰሉ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ቀዳሚ ተጠሪ የሆነው በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴው፣ የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ እና ቁጥራቸው ዐሥራ ሥድስት የሚሆኑት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ የሚገኙት የወዳጅነት ቡድኖች፣ በተለይም በሕዳሴ ግድብ ዙሪያ ከጎረቤት አገራት አንስቶ እስከ ባሕር ማዶ ያሉ አደናቃፊ አገራትን እና ተቋማትን አገራዊ ተጽዕኖ ለመክላት በኹለትዮሽም ሆነ በባለብዙኋን መድረኮች ላይ ይሄ ነው የሚባል ዲፕሎማሲያዊ አበርክቶ አድርገዋል።

- በሰብዓዊ ዕርዳታዎች እና ድጋፎች፣ በመዋዕለ-ንዋይ ፍሰት አልፎም በተለያዩ ማኅበራዊ ልማቶች ዙሪያ፣ ነባር አገራዊ እና ተቋም ተኮር ትስስሮሾችን ከማጥበቅ አንስቶ፣ አዳዲስ መዳረሻ ለመፍጠርም ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲው በጎ ሚናውን መወጣቱን መገንዘብ አይከብድም።

- እንደራሴዎቹ፣ የዴሞክራሲ ቅቡልነትን የተላበሰ ተቋም አባላት መሆናቸውን በመንተራስ፣ እንደ አገራዊ ምክክር መሰል ፋይዳ ያላቸው ጥረቶችን ለአቻዎቻቸው እና ሌሎች አገራት በማብራራት በኩልም ያደረጉት አስተዋጽዖ፣ በተለይም በዚኹ ጉዳይ ላይ የፌድራሉ መንግሥት ዲፕሎማሲያዊ ይኹንታዎችን እንዲያገኝ መታተራቸው አንዱ የእንደራሴዎቹ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ በጎ ገጽ ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል።

- እጅጉን በመጨረሻ ሊባል የሚገባው ባይሆንም ቅሉ፣ ቢያንስ ለጠቅስናቸው ዐራት ዓመታት ያከናወኗቸው ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲዎች፣ ቀረን ብለው ለሚያስቧቸው ይኸው እንቅስቃሴዎቻቸው ክፍተቶቻቸውን ለማየት እና ዕርምቶችን ለመውሰድም ያገኟቸውን ልምዶች መጠቀማቸውን፣ ቢያንስ ከምክር ቤቱ የተገኙ መረጃዎች ከፊል ጥቁምታ ይሰጣሉና፣ አንዱ የእንደራሴዎቹ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ተጠቃሽ ገጽ ነው ብላ ብሪጅ ታምናለች።

## ተግዳሮቶች

- ተቋማዊ የአቅም ውስንነት፦ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲዉን ይተገብራሉ ብለን ከላይ ያነሳናቸው አካላት በዋናነት የውጭ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ እና ዐሥራ ሥድስት የሚሆኑት የምክር ቤት የወዳጅነት ቡድኖች በጥልቀትና በብቃት የሚደግፍ በቂ የሰለጠነ ባለሙያ (ኤክስፐርት) ወይም ሠራተኛ አለመኖር፣ አንዱ ተግዳሮት ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል።
- እንደራሴዎቹ፣ በዚኽ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ተግባሮቻቸው ብሔራዊ ጉዳዮችን ብቻም ሳይሆን፣ ከዙሪያ ገባው የአፍሪካ ቀንድ እና ቀጠናዊ ተለዋዋጭ የኃይል አሰላለፍ አንስቶ እስከ ጂዖ ፖለቲካ እና ዓለም ዓቀፍ ሕግጋት ድረስ ጥልቅ መረዳት እንዲኖራቸ መጠበቁ ዕሙን ነው፤ ይኽን መሰሉ ዐቅም ደግሞ ከሚደራጅባቸው አማራጮች አንዱ፣ ተከታታይነት ያለው አጀንዳ ተኮር ሥልጠና ማግኘት መሆኑንም መገንዘብ አይከብድም፤ እናም፣ በእነዚኽ ርዕሰ-ጉዳዮች ዙሪያ በቂ ሙያዊ ሥልጠና አለመሰጠቱ፣ ዲፕሎማሲያዊ ተግባራቸውን እንደራሴዎቹ በሚፈልጉት ልክ እንዳያከናውኑት ማድረጉ አንዱ ተግዳሮታቸው ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል።
- የኢትዮጵያ እንደራሴዎች እንደ ኬንያ ከመሳሰሉ ጎረቤት አገራት አንስቶ በሌሎች አገራት በአቻዎቻቸው ከሚተገበሩት ፓርላመነታዊ ዲፕሎማሲዎች ቁጥሮች አኳያ፣ በትንሹ ወደኋላ ቀረት ያሉ ይመስላል፤ ለዚኽ የተለያዩ ምክያቶች ሊኖሩ ቢችሉም፣ በቁጥር በዛ ያሉ ዲፕሎማሲዎችን ቢተገብሮ ኖሮ ከዚኽ የተሻለ አፈጻፀም ሊያሳዩ እንደመቻላቸው፣ ይኽም በተግዳሮትነት ሊነሳ ይችላል።
- እንደራሴ ባደረገችው ዳሰሳ እንደተረዳቸው፣ ምክር ቤቱ የአፍሪካ፣ ካሪቢያንና ፓስፊክ (ACP) እና አውሮፓ ህብረት፣ ኢንተር ፓርላማንታሪ ዩኒየን (IPU)፣ ፓን አፍሪካን ፓርላመንት (PAP)፣ እና የአፍሪካ ፓርላመንታዊ ዩኒየን ባሉ ባለ ብዙ ወገን የዲፕሎማሲ መድረኮች ላይ በንቃት እየተሰተፉ ይገኛል። ይሁን እንጂ፣ በኢትዮጵያ ሐሳብ አመንጪነት በአዲስ አበባ እ.ኤ.አ በ2004 ዓ.ም. የተመሰረተው እና ጽህፈት ቤቱም አዲስ አበባ የሚገኘው የኢጋድ አባል አገራት ኢንተር ፓርላማንታዊ ዩኒየን የተመሰረተበትን ዓላማ በሚመጥን መልኩ እስካሁን የጎላ እንቅስቃሴ ሳያደርግ መቅረቱ፣ ይህ ሁኔታም የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ብቻ ጉዳይ ባይሆንም፣ እንደ ሀሳብ አመንጪ እና መቀመጫ የፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ሥራ ድክመት ሊቆጠር የሚችል ተግዳሮት ነው።

## ምክረ-ሐሳባዊ ነጥቦች

- እንደራሴዎቹም ሆኑ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲዎቹን በቀጥታ እንዲተገብሩ ኀላፊነት የተሰጣቸው ከላይ የጠቅስናቸው አካላት፣ በታላቁ ሕዳሴ ግድብ ዙሪያ ያደረጉት አስተዋጽዖ አሌ የሚባል አይደለም፤ በእርግጥ በዚኹ ግድብ ዙሪያ ገና ብዙ የሚሠሩ ዲፕሎማሲያዊ ሥራዎች ከመኖራቸው አኳያም፣ ተጨማሪ ምናልባትም በተለዩ ገጾች መፈጸም የሚያሻቸው ዲፕሎማሲያዊ ሥራዎች ይቀሯቸዋልና፣ ሂደቱ በሚፈልገው ልክ ይሄዱበታል ብላ ብሪጅ ታምናለች። ከዚኽ ባለፈ ግን፣ አኹን ደግሞ አንድ ወሳኝ ዲፕሎማሲያዊ ዕጥፋት ላይ ራሳቸውን እንዳገኙት ግልጽ ነው፤ ይኽም፣ የኢትዮጵያ የባሕር በር ይገባኛልነት እና ተያያዥ ፍትሓዊ የወደብ ጥያቄ ነው። ከዚኽ አንፃርም፣ አስቀድሞ በግድቡ ዙሪያ ካደረጓቸው የማሳመን ጥረቶች ስኬቶች እና ተግዳሮቶች በመነሳት ለዚኽ ወሳኝ አገራዊ ጉዳይ ከዚያኣ የበለጠ ዝግጁነት እንደሚጠብቃቸው የአደባባይ እውነት ነው፤ እናም፣ የሚመለከታቸው እኒኹ አካላት እንደ ብሪጅ ከመሳሰሉ አገር በቀል ተቋማት ጋር በተጨባጭ ጥናታዊ ጹሑፎች ዙሪያ ድጋፎች እንዲያገኙ በማድረግ፣ ለዚኽ የመጨረሻ የሥራ ዘመናቸው ግዙፍ ሥራቸውን ለመከወን ካደረጓቸው የበለጡ ሰፊ ዝግጅቶች ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ብሪጅ አበክራ ማሳሰብ ትሻለች።
- ከላይ በተጠቀሰው የባሕር በር ይገባኛልነትም ሆነ በሌሎች ወቅት ተኮር እና ሰንባች አገራዊ ጉዳዮች ላይ፣ እንደራሴዎቹ ከሄዱበት መንገድ ይበልጥ አትራፊ ዲፕሎማሲዎችን እንዲከውኑ፣ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አባላትን ባልተቋረጠ መልኩ ማወያይት ይኖርባቸው ብላ እንደራሴ ታምናለች፤ ለዚኽም ተጨማሪ ዲጂታል መሰል ዲያስፖራውን መድረሻ አማራጮችን ጨምሮ፣ ሌሎች አማራጮችን አብዝተው እንዲጠቀሙ ማስታወስ አስፈላጊ ይመስለናል።

- የተጠናቀቀው የሕዳሴው ግድብም ሆነ፣ በቀጣይ ኢትዮጵያ የምትሻው ወደብ፣ አገሪቷ ከጎረቤቶቿ እና ከሌሎች ወዳጅ አገራት ጋር እያደገ የሚሄድ ኢኮኖሚያዊ ትስስሮሽችን ለመፍጠር ጭምር ያለመ ከመሆኑ አኳያ፣ እንደራሴዎቹም ይኽን ርዕሰ-ጉዳይ፣ በቀጣይ የፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲው ተግባራቸው አንዱ አዕማድ ያደረጉት ዘንድ ብሪጅ ማስታወስ ትፈልጋለች።

- እንደራሴዎቹ፣ በኹለትዮሽም ሆነ በብዙኃን መድረኮች ደረጃ ለመንግሥትን የውጭ ፖሊሲ አፈጻጸም ድጋፍ ሲያሰባስቡ መክረማቸውን መረዳት ብዙም አይከብድም፤ ነገር ግን፣ አኹን ከዚኽ የተሻሉ ድጋፎችን በተለይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ካላቸው ጠንካራ ምጣኔ ሀብታዊ ደረጃ አኳያ ኢትዮጵያ ላይ ተጽዕኖ ያስራፋሉ በሚባሉ አገራት እና ተቋማት ዘንድ ማሰባሰቡን አጠናክረው ይቀጥሉ ዘንድ ብሪጅ ጥሪ ማድረግ ትሻለች።

- ለዚኽ መሰሉ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ፣ ሉላዊ ፖለቲካውንም ሆነ ዙሪያ ገባውን የጎረቤት አገራትን ተለዋዋጭ ማኅበረ-ፖለቲካ በቅጡ መረዳት እጅጉን አስፈላጊ መሆኑ አሌ አይባልም፤ ከዚኽ አንጻርም፣ እንደራሴዎቹ ይኽን መሰሉን ዐቅም በራሳቸው ብቻ እንዲያደርጉት በፍጹም አይጠበቅምና፣ በእነዚኽ ርዕሰ-ጉዳዮች ዙሪያ ያልተቋረጡ ተከታታይ ሙያዊ ሥልጠናዎች የሚያገኙባቸው መንገዶችን ማፈላለግ እና ዓለም አቀፍ ጉዳዮችን ለመተንተን የሚያስችሉ ብቃት ያላቸው የምርምር ባለሙያዎችን በሚቻለው ልክ መቅጠር ለነገ ማደር ያለበት ጉዳይ እንዳይሆን ስትል እንደራሴ ማሳሰብ ትፈልጋለች።

- እንደራሴዎቹ፣ በዚኽ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ተግባራት ዙሪያ በብዙኃን መድረኮች እንደመሳተፋቸው፣ ከሚያገኟቸው ጠንካራ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ገንብተዋል ከሚባሉ አገራት የሚያገኟቸውን ልምምዶች፣ ወደ አገራቸውም በመውሰድ፣ ኢትዮጵያ በጎደሏት ቦታዎች ላይ የሚሞሉባቸው ኹኔታዎች እንዲኖሩ የእንደራሴነት ኀላፊነታቸውን ይወጡ ዘንድም፣ እንደራሴ አለማስታወስ አይቻላትም።

- በመጨረሻም፤ ኢትዮጵያ እስከአኹን ካሏት ወዳጅ አገራት ከቁጥርም ከጠቀሜታ አኳያም እንዲበዙላት መፈለጓ ዕሙን ነው፤ ስለሆነም፣ እንደራሴዎቹ፣ በቀጣዩ የመጨረሻ ዓመተ-እንደራሴነታቸው የሚያገኟቸውን የኹለትዮሽ እና ባለብዙ መድረኮችን በማስፋፋት ላይ ከቀደመው ጊዜ በላይ አትኩሮት ቢሰጡት አገራዊ ፋይዳው ብዙ ነው ብላ ብሪጅ ታምናለች።

## እንደ መውጪያ

የኢትዮጵያ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ፣ አገሪቱ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ያላትን አቋም ለማጠናከር ወሳኝ ዲፕሎማሲያዊ መሣሪያ ሆኖ ብቅ ካለ ዓመታትን ተሻግሯል። በተለይም በድህረ-ኢሕአዴግ ፖለቲካዊ ሥርዓት፣ በዚኽ የዲፕሎማሲ ሂደት የተገኙት ውጤቶች ተስፋ ሰጪ መሆናቸውን መቀበል አይቸግርም። ያም ሆኖ፣ እንደራሴዎቹ፣ ከላይ በአጭሩ ያነሳሳናቸውን ውስጣዊ እና ውጫዊ ተግዳሮቶቻቸውን በሚቻለው ሰዋዊ እና ቁሳዊ ዐቅም በተቻለ ፍጥነት መሻገር ከቻሉ፣ ከታዩት ስኬቶች በላይ ማሳካት እንደሚ ችሉ ግልጽ ነው። በመሆኑም፣ የእንደራሴዎቹን ምክር ቤት ተቋማዊ ዐቅም ይበልጥ ከማጠናከር አንስቶ ፣ የዲያስፖራውን ተሳትፎ በማስፋት እና በጂዖፖለቲክስ ላይ የተመሰረተ ተከታታይ ሥልጠና በመስጠት፣ የፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲያዊ ተፅዕኗቸውን በቀጠናዊ እና ዓለም ዓቀፍ መድረኮች ላይ የበለጠ እንዲያድግ ማድረግ፣ ለኢትዮጵያ ዘላቂ የውጭ ፖሊሲ ትግበራ ስኬት እጅጉን አኹናዊነት ያለው አስፈላጊ ክንውን ነው። የሚመለከታቸው የፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲው ተጠሪዎችም፣ በውጭ ጉዳይ ፖሊስ ክንዋኔ ላይ ያላቸውንን ሚና የበለጠ ማጠናከር ይኖርባቸዋል። በዚኽም፣ ብሔራዊ ጥቅሞችን የሚያስጠብቁ እና የአገሪቱን ሉዓላዊነት የሚያከብሩ የውጭ ፖሊሲዎች ከዚኽ ይበልጥ በየትኞቹም የሩቅ እና የቅርብ አገራት ዘንድ መድረክ እንዲያገኙ ማድረግ የሚያስችሉ ኹኔታዎችን መፍጠር ያስችላል።

# እንድራሴ

እንድራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

**ከራስ ውርድ፦**

“በእነዚኽ ወርኃዊ የእንደራሴዎቹ ጥቅንሮች ውስጥ ያሉት ኹሉም የገጸ-ሰብ እና የገጸ-መስኮች ምስሎች የተገኙት ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ይፋዊ የመረጃ ምንጮች ነው፤ እንዲኹም፣ ኹሉም ቁጥራዊ ዘገባዎች የተወሰዱትም ከዚኽ ምንጭ ነው። ዳሰሳዊ ምልከታዎቹ፣ አጠቃሎዎች እና ተያያዥ ትንታኔዎቹ የተቋማችን ናቸው።”

# እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

**BRIDGE** Research & Innovation for Democratic Governance and Enhanced Peace

+251 115 57 74 96

+251 911 86 12 34

research@bridge-et.org

https://bridge-et.org/

150096, Addis Ababa, Ethiopia.

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.